# የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ (ረቂቅ)

# ETHIOPIA
# TRANSITIONAL JUSTICE IMPLEMENTATION ROADMAP (DRAFT)

የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር

ሰኔ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


1. መግቢያ 3
2. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ ጠቀሜታ እና አላማ 3
3. የትግበራ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ሂደት እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ 4
4. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ የሚሸፍናቸው ጉዳዮች (ወሰን) 4
5. በፍኖተ-ካርታው ላይ የተመላከቱ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ስራዎች የሚመሩባቸው መርሆች 5
6. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የተቀናጀ ተቋማዊ አመራር 5
   6.1. አላማ እና አስፈላጊነት 5
   6.2. የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ 5
   6.3. የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ 6
   6.4. የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ እና ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ መድረክ በጀት 7
7. በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የሚከናወኑ የትግበራ ስራዎች ተመጋጋቢነት እና ቅደም-ተከተልን የሚመለከቱ ጉዳዮች 9
   7.1. በሽግግር ፍትህ ስራዎች መካከል ውድድር ለማስቀረት/ተመጋጋቢነት ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራት 9
   7.2. የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል ጥቅል እቅድ 9
8. ህዝባዊ ገፅታ የማላበስ/የማንቃት እና መደበኛ የህዝብ ግንኙነት ስራዎች የሚከናወኑበት አግባብ 10
9. የህግ ማውጣት/ማሻሻያ ስራዎች 15
   9.1. መግቢያ 15
   9.2. አዲስ የህግ ማእቀፍ የሚወጣላቸው/የህግ ማሻሻያ ስራ የሚያስፈልጋቸው ዋና ዋና ርእሰ-ጉዳዮች 15
   9.3. የህግ ማርቀቅ/ማሻሻያ ስራ የሚከናወንበት አግባብ እና የጊዜ ሰሌዳ 15
10. የሽግግር ፍትህ ተቋማት አደረጃጀት 16
   10.1. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ስራዎች የሚያከናውኑ ተቋማት ዝርዝር 16
   10.2. የሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋም ስራ የሚከናወንበት አግባብ እና የጊዜ ሰሌዳ 18
   10.3. የተቋማት አቅም ግንባታ ስራ 20
11. በሽግግር ፍትህ ትግበራ የክልሎችን ተሳትፎ እና ሀላፊነት ለመለየት/ለማሳለጥ የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች 24

11.1. መግቢያ 24

11.2. ክልሎች በሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ የሚኖራቸው ሀላፊነት 24

11.3. የባህላዊ ፍትህ ስርዓቶች ሚና 25

12. ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በትግበራ ሂደት የሚኖራቸውን ሚና ለመለየት/ለማስፈፀም የሚከናወኑ ተግባራት 26

13. ለፆታ ጥቃት ሰለባዎች ልዩ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት የሚተገበሩ ተጨማሪ እርምጃዎች 27

14. የሽግግር ፍትህ ትግበራን የሚመለከቱ አገራዊ መረጃዎች የሚያዙበት፣ የሚደራጁበት እና ተደራሽ የሚሆኑበት የመረጃ ቋት ስርዓት 28

አባሪ 1: የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል አጠቃላይ እቅድ (Sequenced Implementation – Master-Deck) 29

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ሥርዐት ግንባታ ስራ ወደ አዲስ ምእራፍ የሚሸጋገርበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ህዳር 2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግስት በወንጀል ተጠያቂነት፣ በእውነት ማውጣት፣ በምህረት፣ በእርቅ፣ በማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያ መርሆች ላይ የተዋቀረ የሽግግር ፍትህ ስርአት ለመተግበር ይፋዊ እንቅስቃሴ መጀመሩ ይታወቃል። በዚህ ውሳኔ ማእቀፍ የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን - ቡድኑ ሰፊ የህዝብ ግብዐት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት በማካሄድ ታህሳስ 19 2016 ዓ.ም **'የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች - የህዝብ ምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት'** ይፋ አድርጓል። በተጨማሪም **'የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ'** ረቂቅ ሰነድ በማዘጋጀት ጥር 2016 ዓ.ም ለመንግስት አስረክቧል።

በቀጣይም የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ከየካቲት 13-17 2016 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በረቂቅ ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር አራት የማጠናቀቂያ ምክክር መርሀ-ግብሮችን አካሂዷል። በዚህ ረጅም፣ አሳታፊ እና አካታች የዝግጅት ሂደት ባለፈ ሰነድ ላይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ30ኛ መደበኛ ስብሰባው ዝርዝር ውይይት ካካሄደ በኋላ ሚያዝያ 9 2016 ዓ.ም **'የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን'** በሙሉ ድምፅ አፅድቋል።

ይህን ተከትሎ ፖሊሲው ወደ ትግበራ ምእራፍ የሚሸጋገርበት የዝግጅት ስራ ተጀምሯል።

ይህ ፍኖተ-ካርታ የተዘጋጀው 'የፖሊሲውን አፈፃፀም፣ ክትትል እና ድጋፍ ሥርዓትን' በተመለከተ ሁሉም የስራ ሂደቶች በሚፈለገው አግባብ እንዲተገበሩ ለማድረግ ዝርዝር አካሄዶችን የሚመራ 'የፖሊሲ አፈፃፀም ፍኖተ ካርታ' የሚዘጋጅ ስለመሆኑ ፖሊሲው ያስቀመጠውን ምልከታ መሰረት በማድረግ ነው።

## 2. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ ጠቀሜታ እና ዓላማ

በኢትዮጵያ ሁሉን-አቀፍ የፖሊሲ ሰነድ መፅደቁ ታላቅ አገራዊ ፍፃሚ ቢሆንም ይህ ብቻውን በቂ ክንውን ሊሆን አይችልም። አገራዊ የሽግግር ፍትህ ስርአት ግንባታን ለማረጋገጥ በቀጣይ ምእራፍ የሚወሰዱ እርምጃዎች ወሳኝ ናቸው።

የሽግግር ፍትህ ትግበራ በባህሪው ከፍተኛ የተቋማት ትብብር፣ ቅንጅት እና የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋትን የሚጠይቅ ነው። በፀደቀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማእቀፍ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም፣ የተሟላ ፍትህ፣ እርቅ እና የህግ የበላይነት የማስፈን ግብ የበርካታ ባለድርሻ አካላትን ሚና እና ሀላፊነት መዘርዘር፣ የስራ ሂደቶቻቸውን እና የጊዜ ማእቀፎችን በግልፅ ማመላከት፣ እና የሀብት አሰባሰብ እና አጠቃቀም ስራ የሚቀናጅበትን አግባብ ማሳየት የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ነው።

በመሆኑም በፖሊሲው ላይ የተመላከቱ ተቋማት ተደራጅተው ስራቸውን እስኪጀምሩ ድረስ፣ እንዲሁም ስራ ከጀመሩ በኋላም ቢሆን ተቀናጅተው እና ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የሽግግር ፍትህ ትግበራን የሚመራ ሁሉን-አቀፍ ፍኖተ-ካርታ አስቀድሞ ማዘጋጀት ተገቢ ነው። የፍኖተ-ካርታ መኖር ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በትብብር እና በተናበበ መንገድ መምራት የሚችሉበትን እድል ይፈጥራል። እንደአገር ውሳኔ ያረፈባቸው የሽግግር ፍትህ አምዶችን በተሻለ ግልፅነት፣ ተገማችነት፣ ወቅታዊነት እና ውጤታማነት መሬት ላይ ለማውረድ እና ለመተግበር ፍኖተ-ካርታ ቁልፍ መሳሪያ ነው።

በቀጣይ ወራት እና አመታት በተለያየ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረግ አጠቃላይ የሽግግር ፍትህ ስርአት ትግበራን የሚመራው ይህ 'የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ' የሚከተሉት ዋና ዋና አላማዎች ይኖሩታል።

- በፖሊሲው ላይ በመመርኮዝ በቀጣይ ተግባራዊ የሚደረጉ ዋና ዋና ስራዎች (activities)፡ ስራዎቹ የሚከናወኑበት የጊዜ ሰሌዳ፡ እና የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶች (outcomes) በዝርዝር ማመላከት፡
- ፖሊሲውን በተገቢ ደረጃ፡ መጠን እና ጥራት ለማስፈፀም የሚያግዙ ሰነዶች እና ዋና ዋና ስራዎች ዝግጅት የሚሳለጥበትን ሂደት/አሰራር (processes/procedures) በዝርዝር ማስቀመጥ፡
- በፖሊሲው የተለያዩ ክፍሎች ትግበራ ሂደት ባለድርሻ ተቋማት የሚኖራቸውን ሚና ወይም ሀላፊነት በግልፅ ማሳየት፡
- በተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና ጊዜያት የሚከናወኑ ቀጣይ ስራዎች በተቀናጀ፡ በተመጋገበ እና ባልተፋለሰ መንገድ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ተግባራዊ የሚደረጉበትን አሰራር መመስረት፡
- ፖሊሲውን ለመተግበር የሚወሰዱ እርምጃዎች አጠቃላይ አፈፃፀም የሚመራበት፡ የሂደቶች አንኳር ፍፃሚዎች በምክክር የሚገመገሙበት እና የጋራ አቅጣጫ የሚሰጥበት ቋሚ ተቋማዊ አሰራር ማመላከት፡
- እንዲሁም ለፖሊሲው ትግበራ የሚያስፈልግ ሀብት ምንጭ፡ የሀብት ዝርዝር፡ እና የመንግስት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሀላፊነትን ማመላከት ናቸው፡፡

## 3. የትግበራ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ሂደት እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

በኢትዮጵያ ለፀደቀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ መሰረት የሆነው አገር-አቀፍ የህዝብ ምክክር እና ግብአት ማሰባበሰብ ስራ - የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ጨምሮ - ከፍተኛ የህዝብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ያረጋገጠ ሂደት ነበር፡፡ የፖሊሲው ረቂቅ የመጨረሻ ቅርፅ የያዘው በተመሳሳይ የህዝብ እይታ እና አስተያየት ሂደት አልፎ ነው፡፡

የዚህ አይነቱ አሰራር መሰረታዊ መልእክት የትኛውንም የሽግግር ፍትህ ክፍልን የሚመለከት የስራ ሂደት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ሙሉ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እና የህዝብን ወሳኝነት በሚያረጋግጥ አግባብ ሊከናወን ይገባል የሚል ነው፡፡

የሽግግር ፍትህን የሚመለከቱ ስራዎችን - ከመሰረታዊ የመሳተፍ ሰብአዊ መብት መርህ ጋር በተጣጣመ አግባብ በዚህ መንገድ ማሳለጥ - በፖሊሲው እና ፖሊሲውን ተከትሎ በሚከናወኑ የትግበራ ስራዎች አንፃር የህዝቡን ሙሉ እምነት ለመግዛት፡ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ ለሰፊው ማህበረሰብ ድምፅ እና የፍትህ እና የሰላም ተስፋ እውቅና ለመስጠት፡ የሂደቱን አጠቃላይ ቅቡልነት ለማስፋት፡ እና ዘለቄታዊ ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም በዚህ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ሂደት ተመሳሳይ የአካታችነት እና አሳታፊነት መርሆች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የመንግስት፡ የህዝብን እና የመብት ጥሰት ሰለባዎችን እይታ እና ድምፅ በተሻለ አግባብ እንዲወከል ለማድረግ የፍኖተ-ካርታው ዝግጅት ስራ ሂደት የቀድሞ የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን አራት አባላትን ጨምሮ፡ ከኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር፡ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፡ ከኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ድርጅት ሀብረት፡ እና ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በተውጣጣ ቡድን እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

## 4. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ የሚሸፍናቸው ጉዳዮች (ወሰን)

ይህ ፍኖተ-ካርታ 'የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን' ለማስፈፀም በየትኛውም መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆነ አካል በሚወሰዱ አሁናዊ ወይም ቀጣይ የህግ፡ የተቋም ወይም የአሰራር ስርአት ወይም ተግባራት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ፍኖተ-ካርታው በብሄራዊ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ማእቀፍ - ክልሎች በአገር-አቀፍ ደረጃ የሚተገበሩ ስራዎችን አስመልክቶ በተሰጧቸው እገዛ የመስጠት፣ የትብብር እና የቅንጅት ግዴታዎች ላይ ሙሉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው አጠቃላይ እሳቤዎች እና መርሆዎች ላይ በመመስረት ስራዎችን የማከናወን ግዴታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ - ክልሎች በአገራዊ የሽግግር ፍትሕ የስራ ሂደት የማይሸፈኑ ጉዳዮችን፣ ጥሰቶችን እና ግጭቶችን በተመለከተ በባለቤትነት በሚያከናውኗቸው ውስን የእውነት ማፈላለግ/ይፋ ማውጣት፣ የዕርቅ እና የማካካሻ ስርዓት ስራዎች ላይ የራሳቸውን ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀት ይችላሉ።

## 5. በፍኖተ-ካርታው ላይ የተመላከቱ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ስራዎች የሚመሩባቸው መርሆች

በፍኖተ-ካርታው ላይ በመመስረት የሚከናወን ማናቸውም የፖሊሲ ትግበራ ሂደት በዓለም-አቀፍ፣ በአህጉር-አቀፍ እና በብሔራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ በተቀመጡ መርሆዎች እና እሴቶች የሚመራ ይሆናል። በመሆኑም በቀጣይ ክፍሎች የተቀመጡ የትግበራ ስራዎች አቀራረፅ እና አፈፃፀም፥

- የተሳታፊዎች እና ተጎጂዎችን ደህንነት በሚጠብቅ፣
- ከዳግም ጥቃት የመጠበቅ መብትን በሚያረጋግጥ፣
- ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በሚያካትት እና በሚያሳትፍ፣
- ተጠያቂነት እና ሁሉን-አቀፍ ፍትህን በሚያሰፍን፣
- ለስርአተ-ጾታ ምልከታ ልዩ ቦታ በሚሰጥ፣
- የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ በሚያስገባ፣
- የተለያዩ የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተቀናጀ፣ በተናበበ እና ቅደም-ተከተልን በጠበቀ አግባብ በሚመራ፣
- ለአገር እና ህዝብ ባለቤትነት እና ውሳኔ ሰጪነት ልዩ ትኩረት በሚሰጥ፣
- እንዲሁም አገራዊ እና አካባቢያዊ ሁነቶችን ግምት ውስጥ በሚያስገባ አግባብ የሚከናወን ይሆናል።

## 6. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የተቀናጀ ተቋማዊ አመራር

### 6.1. ዓላማ እና አስፈላጊነት

በተለያዩ የጊዜ ማእቀፎች የሚከናወን አገራዊ የሽግግር ፍትህ ስራ የብዙ ተቋማትን ትብብር እና ቅንጅት የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ነው። የተቋማት ቅንጅታዊ ግንኙነት እና አሰራር ሲታሰብ በሁለት ምእራፍ በሚከፈሉ የስራ ሂደቶች - የተለያዩ ተቋማዊ አደረጃጀቶች የሚኖራቸውን ተግባርና ሀላፊነት መዘርዘር ተገቢ ይሆናል።

የመጀመሪያው በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ የተመላከቱ ተቋማት በህግ እስኪቋቋሙና ኃላፊነቶቻቸውን ሙሉ ለሙሉ እስኪረከቡ ድረስ ባለው የጊዜ ማእቀፍ ውስጥ የሚከናወኑ የትግበራ ስራዎችን በጊዜያዊነት የሚከታተል እና የሚያስተባብር 'የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ' (Transitional Justice - Ad-hoc Institutional Coordination Mechanism) ነው።

ሁለተኛው በፖሊሲው የተመላከቱ አዳዲስ የሽግግር ፍትሕ ተቋማት ከተቋቋሙ በኋላ አጠቃላይ የትግበራ ሂደቱን አፈፃፀም በዘላቂነት የሚያቀናጅ እና የሚከታተል፣ ሂደቱን እየገመገመ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ፣ እና በትግበራ ሂደት በተቋማት መካከል የሚነሱ ልዩነቶች/አለመግባባቶች የሚፈቱበት 'የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ' (Transitional Justice - Standing Institutional Coordination Mechanism) ነው።

### 6.2. የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ

የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ በየተቋማቱ ከፍተኛ አመራሮች የሚወከሉ 14 አባላት ይኖሩታል።

- አባላቱ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከሰላም ሚኒስቴር፣ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (3) እና ከቀድሞው የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን አባላት (4) የሚውጣጡ ይሆናል።
- መድረኩ ከአባላቱ ውስጥ በፍትሕ ሚኒስቴር የሚሰየም አንድ ሰብሳቢ እና ፀሀፊ ይኖሩታል።
- በፍትሕ ሚኒስቴር የሚገኘው የሰብአዊ መብቶች ክትትል ዳይሬክቶሬት የአደረጃጀቱ ሴክሬታሪያት በመሆን ያገለግላል።

የዚህ አደረጃጀት **የቆይታ ጊዜ** አዲስ የሚመሰረቱ የሽግግር ፍትሕ ተቋማት እስከሚቋቋሙበት እና የሽግግር ፍትሕ ትግበራን በዘላቂነት በሚከታተል ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ እስከሚተካበት ጊዜ ይሆናል።

- ሆኖም የዚህ አደረጃጀት የቆይታ ጊዜ ከአምስት ወራት (ህዳር 2017 ዓ.ም) በላይ አያልፍም።

'የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ' የሚከተሉት ዝርዝር ሀላፊነቶች ይኖሩታል፡

- በፖሊሲው ላይ ተግባርና ኃላፊነት በተሰጣቸው ነባር ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡
- በፌዴራል እና በክልል የሽግግር ፍትሕ ተቋማት መካከል ተገቢ ቅንጅታዊ አሰራር እና ትብብር እንዲመሰረት ያደርጋል፡ እንዳስፈላጊነቱ ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡
- ለሽግግር ፍትሕ የተቀናጀ ትግበራ የሚያስፈልጉ ጥናቶች በባለሙያዎች ተዘጋጅተው ሲቀርቡ ይገመግማል፡ ምክረ-ሀሳብ ይሰጣል፡ የጋራ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡
- አዲስ የሚቋቋሙ የሽግግር ፍትሕ ተቋማት የማቋቋሚያ ሕጎች ረቂቅ እና የአሰራር ሥርአት ሰነዶች (ደንቦች፣ መመሪያዎች ወዘተ) በባለሙያዎች ተዘጋጅተው ሲቀርቡ ይገመግማል፡ ምክረ-ሀሳብ ያቀርባል፡ የጋራ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡
- አዲስ የሚቋቋሙ የሽግግር ፍትሕ ተቋማት በፍኖተ-ካርታው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ማእቀፍ ውስጥ መቋቋማቸውን እና መደራጀታቸውን ይከታተላል፡
- በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ የህዝብ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን ይከታተላል፡ መሰራታቸውን ያረጋግጣል፡
- በተለያዩ አካላት የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች እንዲሰሩ ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፡
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አዲስ ለሚቋቋሙ ተቋማት ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች እና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች የግንዛቤ ፈጠራ እና አቅም ግንባታ ስልጠናዎች እንዲዘጋጁ/እንዲሰጡ ያደርጋል፡
- ለግንዛቤ ፈጠራ እና ስልጠና ስራ የሚገለግሉ ማንዋሎችና ሰነዶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡

የአደረጃጀቱን ውስጣዊ አሰራር የሚገዛ ዝርዝር መመሪያ የፍትሕ ሚኒስቴር ያወጣል።

### 6.3. የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ

'የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ' በየተቋማቱ ከፍተኛ አመራሮች የሚወከሉ 13 አባላት ይኖሩታል።

- ይህም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከሰላም ሚኒስቴር፣ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ወደፊት ከሚደራጁ አራት ተቋማት (ከሁሉም አንድ አንድ)፣ እና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (3) የሚወከሉ አባላትን የሚያካትት ይሆናል።
- አደረጃጀቱ ከአባላቱ መካከል የሚሰየሙ ሰብሳቢ እና ፀሀፊ ይኖሩታል።
- በፍትሕ ሚኒስቴር የተደራጀው የሰብአዊ መብቶች ክትትል ዳይሬክቶሬት የአደረጃጀቱ ሴክሬታሪያት በመሆን ያገለግላል።

የዚህ አደረጃጀት የቆይታ ጊዜ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ስራ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ይሆናል።

የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ የሚከተሉት ዝርዝር ሀላፊነቶች ይኖሩታል።

- በፖሊሲው መሰረት ተግባርና ኃላፊነት በተሰጣቸው ተቋማት መካከል በሀገር-አቀፍ ደረጃ ዘላቂ ቅንጅታዊ አሰራር እና ትብብር እንዲመሰረት ያደርጋል፣
    - አንድ ወጥ አተገባበር እንዲኖር የሚያስችሉ ስራዎችን ያከናውናል፣
    - ቅንጅታዊ አሰራሩ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፣ አስፈላጊ ድጋፍ ያደርጋል፣
- በየጊዜው የአደረጃጀቱን እይታ የሚሹ ወይም አቅጣጫ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ሲኖሩ የጋራ ምክክር በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
- ለሽግግር ፍትሕ ትግበራ የሚያስፈልጉ ጥናቶች ሲቀርቡ ይገመግማል፣ ምክረ-ሀሳብ ይሰጣል፣
- በፌዴራል እና በክልል የሽግግር ፍትሕ ተቋማት መካከል ተገቢ ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር እንዲኖር ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣
- የተቋማትን ነፃነት ሳይነካ በፖሊሲው መሰረት ተግባርና ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት ስራቸውን እያከናወኑ መሆኑን ይከታተላል፣ ተገቢ ድጋፍ ይሰጣል፣
- በተቋማት በተናጠል የሚሰሩ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆኖ - በፖሊሲው እና በትግበራ ስራዎች ላይ የሚሳለጡ ዘላቂ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን በሀገር-አቀፍ ደረጃ ያስተባብራል፣ ይመራል፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አዲስ ለሚቋቋሙ ተቋማት ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች እና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች የግንዛቤ ፈጠራ እና አቅም ግንባታ ስልጠናዎች እንዲዘጋጁ፣ እንዲሁም ለግንዛቤ ፈጠራ የሚያገለግሉ ሰነዶች እንዲደራጁ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
- የሽግግር ፍትህ ተቋማትን ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና አሰራር ባከበረ መልኩ በዚህ ፍኖተ-ካርታ ላይ የተመለከተው ጥቅል የክትትልና ግምገማ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ መተግበሩን ይከታተላል፣

የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት በየሶስት ወሩ እየተገናኘ በሽግግር ፍትህ ሥራ ሂደቶች ላይ ውይይት ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ እንደአግባብነቱ ውሳኔዎች እና ቀጣይ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣ አስቀድሞ የተሰጡ የጋራ ውሳኔዎች መተግበራቸውን ይከታተላል።

### 6.4. የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ እና ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ በጀት

የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ እና ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረኮች የስራቸውን ስፋት እና ባህሪ ባገናዘበ መልኩ ተግባርና ኃላፊነቶቻቸውን ለመወጣት የሚያስችል በቂ በጀት ይኖራቸዋል።

- በጀቱ በመንግስት ከሚመደብ ገንዘብ፣ ከሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች እና አጋር አካላት የሚገኝ የገንዘብ እና የአይነት ድጋፍ፣ እንዲሁም ከሌሎች በሕግ ከሚወሰኑ ምንጮች የሚገኝ ይሆናል።

- የገንዘብ ሚኒስቴር በአገር-አቀፍ ደረጃ የሽግግር ፍትህ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በቂ በጀት ይመድባል፡፡
- የተቋማት ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት የሽግግር ፍትህ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የገንዘብ እና የአይነት ድጋፍ ማግኘት እንዲቻል ከተለያዩ አለምአቀፍ እና አገር-አቀፍ አጋር አካላት ጋር በቅርበት ይሰራል፡ ሀብት ያሰባስባል፡፡
- የሽግግር ፍትሕ የትግበራ ምዕራፍ የፋይናንስ እና የግዢ አገልግሎቶች የመንግስት ፋይናንስ እና ግዢ ሕግን፡ የአደረጃጀቶቹን ልዩ ባህሪ፡ እና የትግበራ ሂደቱን ውስብስብነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ የሚፈፀም ይሆናል፡፡
- የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረኮች በጀት የፍትህ ሚኒስቴርን የፋይናንስ እና ግዢ ክፍል የአገልግሎት መሰረተ-ልማት የሚጠቀም ይሆናል፡፡
- የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ እና ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረኮች አጠቃላይ አመታዊ በጀት ብር ____________________ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በሚቀጥሉት ክፍሎች ይቀርባል፡፡

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ተቋማዊ ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ[1] | ለትግበራ የሚያስፈልግ በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ መመስረት | ፍትሕ ሚኒስቴር | ምእራፍ 1: (ሰኔ 15 2016 ዓ.ም) | |
| 2 | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ መደበኛ ስብሰባዎች ማካሄድ (2) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት | ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ መድረክ ከተመሰረተ በኋላ (ከሰኔ 2016 እስከ ህዳር 2017 ዓ.ም) | |
| 3 | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ መመስረት | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2: ጥቅምት 15 2017 ዓ.ም (ቢያንስ ከቋሚ የሽግግር ፍትህ ተቋማት ውስጥ አንዱ ወደስራ ሙሉ ለሙሉ በገባ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ) | |
| 4 | የሽግግር ፍትህ ስራዎች በተመለከተ የጋራ ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 5 | መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎች ማካሄድ (4) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | መስከረም-ነሐሴ 2017 ዓ.ም | |
| 6 | የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መደበኛ የመስክ ክትትል ስራ (4) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2-5: (መስከረም-ነሐሴ 2017 ዓ.ም) | |
| | | | | |

[1] በሚቀጥሉት አስራ-አምስት ወራት የጊዜ ማእቀፍ ላይ የሚያተኩሩት የትግበራ ስራዎች በአምስት የተለያዩ ምእራፎች ተከፋፍለው የሚከናወኑ ይሆናል፡፡
ምእራፍ 1 (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ ምእራፍ 2 (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ ምእራፍ ሶስት (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ ምእራፍ አራት (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ እንዲሁም ምእራፍ አምስት (ከሰኔ-ነሃሴ 2017 ዓ.ም) ያለውን ጊዜ የሚሸፍኑ ይሆናል፡፡

## 7. በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የሚከናወኑ የትግበራ ስራዎች ተመጋጋቢነት እና ቅደም-ተከተልን የሚመለከቱ ጉዳዮች

### 7.1. በሽግግር ፍትህ ስራዎች መካከል ውድድር ለማስቀረት/ተመጋጋቢነት ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራት

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ የሚፈለገውን ግብ እንዲያሳካ ይዘቱን ሁሉን-አቀፍ በሆነ መንገድ መቅረፅ ብቻ ሳይሆን - የሚተገበሩ የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስልቶች በተመጋገበ፣ በተቀናጀና ተገቢ ቅደም-ተከተልን በሚጠብቅ አግባብ መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

የሽግግር ፍትህ ሂደት ተግባር በርካታ ተቋማትን የሚያሳትፍ እንደመሆኑ መጠን - በፍኖተ-ካርታው እና በቀጣይ በሚወጡ ህጎች ላይ በትግበራ ሂደት አንዱ የሽግግር ፍትህ ስልት ከሌላው ስልት ጋር የሚኖረውን መስተጋብር እና መደጋገፍ መለየት፣ እንዲሁም ለዚህ የሚያስፈልገውን አሰራር በግልፅ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንፃር የሽግግር ፍትሕ አላባዎች ትግበራ በተመጋገበ እና ሚዛናዊ ቅደም ተከተልን በጠበቀ አግባብ ለማሳለጥ የሚከተሉት ተጨማሪ ስራዎች ይከናወናሉ።

- በተቋማት መካከል ተመጋጋቢ፣ ተደጋጋፊ እና የተቀናጀ (complementary, mutually supportive, coordinated) የስራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል አሰራር (ገላጭ ሰነድ) ከጅምሩ ይዘረጋል፣
- የሽግግር ፍትህ ስራዎች በአገር-አቀፍ ደረጃ ከሚተገበሩ ሌሎች ተዛማጅ የሪፎርም ስራዎች እና ፕሮግራሞች፣ በተለይም ከሰላም ግንባታ፣ የፍትህ እና ፀጥታ ዘርፍ ማሻሻያ፣ የቀድሞ ተዋጊዎች ትጥቅ ማስፈታት እና ማቋቋም፣ እና የሀገራዊ ምክክር ስራዎች ጋር የሚኖረውን መስተጋብር የሚያሳይ እና ቀጣይ ሂደቶችን የሚመራ ሰነድ ይዘጋጃል።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | ለትግበራ የሚያስፈልግ በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በሽግግር ፍትህ ተቋማት መካከል ተመጋጋቢ፣ ተደጋጋፊ እና የተቀናጀ የስራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል አሰራር (ገላጭ ሰነድ) ዝግጅት፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 1፡ ሐምሌ 15 2016 ዓ.ም | |
| 2 | የሽግግር ፍትህ ስራዎች በአገር-አቀፍ ደረጃ ከሚተገበሩ ሌሎች ተዛማጅ የሪፎርምና ስራዎች ጋር የሚኖራቸውን መስተጋብር የሚተነትን፣ ቀጣይ ሂደቶችን የሚመራ ገላጭ ሰነድ ዝግጅት፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 1፡ ሐምሌ 15 2016 ዓ.ም | |
| | | | | |

### 7.2. የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል ጥቅል እቅድ

በሽግግር ፍትህ ስራዎች መካከል - አላባዎቹ ከሚኖራቸው አንፃራዊ ተፅእኖ ወይም ውጤት ጋር በተያያዘ የሚመሰረት የተለየ ማበላለጥ አይኖርም፡፡ በፖሊሲው ላይ በግልፅ እንደተንፀባረቀው - በዚህ ረገድ ተመራጩ አካሄድ የሽግግር ፍትህ የተለያዩ ስራዎችን በአንድ ሁሉን-አቀፍ የፖሊሲ ማእቀፍ ማካተት እና መተግበር ነው።

ይሁን እንጂ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማእቀፍ ማዘጋጀት ማለት የግድ ሁሉንም ተግባራት ባንድ ጊዜ ማከናወን ይገባል ማለት አይደለም፡፡ የሽግግር ፍትህ የተለያዩ አምዶች ትግበራ ቅደም-ተከትል ውሳኔ - በዋናነት መሬት ላይ ያሉ እውነታዎችን፣ የፀጥታ ሁኔታዎችን፣ በፖለቲካ ምህዳሩ የሚገለፁ ቀጣይ ማረጋገጫዎችን፣ የረጅም ጊዜ ጥቅሞችን/ግቦችን፣ የሀብት ዝግጅት እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሌሎች ተግዳሮቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ጭምር የሚከናወን ነው።

በሁሉም የሽግግር ፍትህ ስልቶች ትግበራ ስራዎች መካከል ተመጋጋቢነት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ - ኢትዮጵያ አሁን ላይ ከምትገኝበት ውስብስብ የግጭት እና የሰብአዊ መብቶች አከባበር አውድ አንፃር ሶስት አንኳር ስራዎች ማለትም፦

- የህዝብ ንቅናቄ/አድቮካሲ ስራዎች፣
- የተቋማዊ አቅም ግንባታ ቅድመ-ዝግጅት ስራዎች፣
- እና የወንጀል ተጠያቂነት፣ የእውነት ማፈላለግ/ማውጣት፣ እና የምህረት ስራ ሂደቶች ልዩ ትኩረት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት ይሆናሉ።

ይህ ልዩ ትኩረት ስልቶቹ አገራዊ እርቅን እና ዘላቂ የሰላም አጀንዳ ለማራመድ እና የተሻለ የዲሞክራሲ ስርአት ሽግግርን እውን ለማድረግ ከሚኖራቸው ሚና (ብቻ) የሚመነጭ ነው።

በመሆኑም የዘላቂ ማካካሻ እና የተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎች በቅደም-ተከተል ደረጃ በቀጣይ የሚከናወኑ ተግባራት ይሆናሉ። ሆኖም ይህ ውሳኔ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚጀመሩ የማካካሻ ስርአት ውስን ክፍሎች አይኖሩም ማለት እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል።

በሌላ በኩል በተለይ የእውነት ማፈላለግና ማውጣት ስራዎችን የሚመሩ የህግ እና ተቋማዊ አደረጃጀቶች ስራ እና የጊዜ ሰሌዳ በሁለት መሰረታዊ ሁነቶች ላይ ተመርኩዞ የሚወሰን ይሆናል።

***በመጀመሪያ ደረጃ*** - ተቋሙ ወደ ሙሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚገባበት የጊዜ ሰሌዳ ውሳኔ በኢትዮጵያ ያለውን ወይም ይኖራል ተብሎ የሚጠበቀውን ተጨባጭ የሰላም እና መረጋጋት ፖለቲካዊ ከባቢ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል። ከዚህ አንፃር በማቋቋሚያ ህግ ደረጃ የተቋሙ ህልው መሆን በጥንቃቄ ወቅታዊ ሁኔታዎችን - በተለይም ለተቋሙ እና ባለሙያዎቹ ያልተገደበ የስራ እንቅስቃሴ እና ህዝብን የመድረስ ስራ አመቺ አገራዊ የሰላም እና ደህንነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ብቻ የሚፈፀም ይሆናል።

***በሁለተኛ ደረጃ*** - ተቋሙ ወደተሟላ ትግበራ የሚገባው የውስጥ አደረጃጀቱ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅና በተሟላ የሰው ሀይል እና የበጀት ቁመና ላይ ሲገኝ ብቻ ይሆናል። ተቋሙን ያለጊዜው እና ያለ በቂ ፋይናንስ እና የሰው ሀብት ዝግጅት በህግ እንዲቋቋም ማድረግ ወደስራ ሳይገባ ለረጅም ጊዜ ስሙን ብቻ ይዞ የሚቀይበትን አሉታዊ ሁነት ይፈጥራል። ይህም በተቋሙ ላይ ህዝቡ የሚኖረውን እምነት ከጅምሩ የሚሸረሽር እና በአጠቃላይ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር ይሆናል።

ለዚህ ፍኖተ-ካርታ አላማ የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስራዎች በቅደም-ተከተል የሚተገበሩበት እና የሚደራጁበት ሁሉን-አቀፍ እቅድ የሚዘጋጅ ይሆናል። የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል አጠቃላይ እቅድ (sequenced implementation - master deck) **በአባሪ 1 ላይ ተመልክቷል።**

## 8. ህዝባዊ ገፅታ የማላበስ/የማንቃት እና መደበኛ የህዝብ ግንኙነት ስራዎች የሚከናወኑበት አግባብ

በሀገር መሪነት እና ሕዝብ ባለቤትነት መርህ ላይ የተዋቀረ የሽግግር ፍትህ ስርአት ግንባታ ሂደት የህዝብ ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ እና ሰፊ ህዝባዊ ድጋፍ የሚያገኝበትን አሰራር የሚቀይስ መሆን አለበት። ይህን ዓላማ ለማሳካት ፖሊሲውን እና የትግበራ ሂደቱን በተደራጀ መንገድ የማስተዋወቅ እና ህዝባዊነት የማላበስ ስራዎችን ማከናወን፣ እንዲሁም አጠቃላይ ሂደቱ በግልፀኝነት መርሆች የሚመራ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ህዝቡ እና ባለድርሻ አካላት ከሂደቱ ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ ስራዎችን በተመለከተ በተደራጀ እና በቀላሉ በሚረዱት ቋንቋ ግልፅ መረጃ የሚያገኙበት አሰራር መዘርጋትም ተገቢ ይሆናል።

በመሆኑም በተቋማት እና ባለድርሻዎች ቅንጅታዊ አሰራር ማእቀፍ - ከኢትዮጵያውያን ፍላጎት፣ ተስፋ እና የጋራ ትልም ጋር የተንሰላሰለ ውጤታማ የሽግግር ፍትህ ስራ ለማከናወን - የፖሊሲውን መሰረታዊ ሀሳቦች፣ ግቦች እና

የሽግግር ፍትህ ተቋማትን ሚና ለህዝብ ግልፅ ማድረግ፡ የሽግግር ፍትህ አንኳር ሰነዶችን በብዙ የአገሪቱ ቋንቋዎች እንዲተረጎሙ እና ተደራሽ እንዲሆኑ፡ እንደአግባብነቱ በትግበራ ዋና ዋና ምእራፎች የህዝብን ተሳትፎ እና የባለድርሻ አካላት ድጋፍ እና የባለቤትነት ስሜት የሚያጠናክሩ ስራዎችን (ህዝባዊ ውይይቶች፡ ስልጠናዎች ወዘተ) ማከናወን፡ በድህረ-ገፅ፡ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እና በፕሬስ ድርጅቶች አማካኝነት ማህበረሰብን የማሳወቅ ተከታታይ ሥራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

የሽግግር ፍትህ ሂደቶችን ህዝባዊነት ከማረጋገጥ፡ ህዝብን ከማንቃቃት እና ውጤታማ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ከማሳለጥ አንፃር የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ/ትግበራ ሂደቶችን አጠቃላይ ስእል የሚሰጥ መሰረታዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ በተለያዩ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፡ (1)<br>በህትመት እና በድህረ-ገፆች ማሰራጨት፡ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 2. | የህዝብ ተሳትፎ ለሽግግር ፍትህ ውጤታማነት ያለውን ሚና የሚያሳይ በህዝብ አስተያየት ላይ የተመሰረተ የቲቪ ፕሮግራም ማዘጋጀት፡ ማስተላለፍ፡ (12) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 3. | በሽግግር ፍትህ አላማ እና ግቦች ላይ የሀገሪቱ ርዕሰ-ብሄር አጭር መልዕክት ተቀርጾ በዋና ዋና ቋንቋዎች በሁሉም ሚዲያዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፡ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡<br>የፕሬዚደንት ጽህፈት ቤት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 4. | በሽግግር ፍትህ አላማ/ግቦች ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ መልዕክት ተቀርጾ በዋና ዋና ቋንቋዎች በሁሉም ሚዲያዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፡ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 5. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ ምዕራፍ ክልሎችና ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች የሚኖራቸውን ሚና የሚገልፅ ዘጋቢ ቪዲዮ ዶክመንታሪ ማዘጋጀት፡ ማሰራጨት፡ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 6. | የእምነት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲን በመተግበር ሂደት በሚኖራቸው ሚና ዙሪያ ተከታታይ አገር አቀፍ የፓናል ውይይቶችን ማካሄድ፡ (3) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ የሀይማኖት ተቋማት ምክር ቤት፡ የክልል መስተዳድሮች፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 7. | ለፌዴራል እና ክልል መንግስት ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ለክልል ምክር ቤት አባላት የፖሊሲውን ይዘት እና የትግበራ ሂደትን በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (14) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከተቋማቱ ጋር በመተባበር | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 8. | በሁሉም ክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ለሚገኙ የዞንና የወረዳ ሀላፊዎች የፖሊሲውን ይዘት/የትግበራ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (28) | ከተቋማቱ ጋር በመተባበር፡ | | |
| 9. | በአዲስ አበባ/በክልል በሰብዓዊ መብት፡ ግጭት አፈታት፡ የሕግ የበላይነትና ፍትህ ጉዳዮች ላይ ለሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ (awareness, briefing) መድረኮች ማዘጋጀት፡ (10) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ ሶስት (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 10. | ለፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች የፖሊሲው ይዘት እና ትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (2) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 11. | በሀገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበረሰብ እና ከፍተኛ አመራር የፖሊሲ ይዘት/ትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (10) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 12. | ለዳያስፖራ ማህበረሰብ ተወካዮች የፖሊሲ ይዘት እና የትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (በአውሮፓ፡ አሜሪካ፡ በአረብ ሀገራት፡ ውስን የአፍሪካ አገራት) (5) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከዳያስፖራ ኮሚሽን እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ከምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 13. | በሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆች እና ሌሎች ህጎች ላይ ህዝብ ዝርዝር አስተያየት የሚሰጥበት ከመደበኛው አሰራር የተለየ አገር-አቀፍ የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት፡ (ለአንድ ረቂቅ ህግ 4 አገር-አቀፍ መድረኮች) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 14. | የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱን፡ የህዝብ ምክክርና ግብአት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት፡ እና የፖሊሲውን አማርኛ እና እንግሊዝኛ ቅጂ በህትመት እና በድህረ-ገፆች ማሰራጨት፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 15. | የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን ትግርኛ፡ ኦሮምኛ፡ አፋርኛ፡ ሲዳምኛ፡ ጉራግኛ እና ሶማሊኛን ጨምሮ ቢያንስ በአስር አገራዊ ቋንቋዎች መተርጎም፡ ቅጂውን በህትመት እና በማህበራዊ ገጾች እና ድህረ-ገፆች ተደራሽ ማድረግ፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ከየክልሎቹ ፍትህ ቢሮዎች ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 16. | የሽግግር ፍትህ ሂደትን የሚመለከቱ ትምህርቶችን/መልዕክቶችን የያዙ አጫጭር ተከታታይ ዘጋቢ ቪዲዮዎችን የሚያዘጋጅ የዘርፉ ባለሙያ መቅጠር፡ ማስማራት፡ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 17. | በስኬታማ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት ያለፉ አገራት ተሞክሮን የሚያሳዩ ታሪካዊ እና ምስላዊ ቅንብር ማዘጋጀት፡ ማሰራጨት፡ (2) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 18. | የሽግግር ፍትሕን የተለያዩ ጉዳዮችን የተመለከቱ ድራማ እና ካርቱን አጫጭር ቪዲዮዎች ማዘጋጀት፣ ማሰራጨት፣ (5) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ከምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 19. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች (ተጎጂዎች፣ የፆታዊ ጥቃት ሰለባዎች፣ ተፈናቃዮች፣ አካል ጉዳተኞች) የሚኖራቸውን ሚና የሚገልፅ ዘጋቢ ቪዲዮ ዶክመንታሪ ማዘጋጀት፣ ልዩ ሁኔታቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ማደራጀት፣ ማሰራጨት፣ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ | ምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 20. | ለሚዲያ ተቋማት የሚሰጡ መረጃዎች አይነት፣ መረጃ ስለሚሰጥበት ጊዜ/አግባብ፣ የመረጃ/የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት፣ መረጃ ስለሚሰጠው አካል፣ እና ከሚዲያ ተቋማት ጋር የሚኖር መደበኛ ግንኙነትን የሚገዛ ሁሉን-አቀፍ የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣ ስራ ላይ ማዋል፣ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 21. | ከሚዲያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በመደበኛነት ምላሽ የሚሰጥ ባለሙያ ማዘጋጀት፣ አከራካሪ እና የብዙሀኑ ሚዲያ ጥያቄ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አንድ ወጥ ምላሽ ማዘጋጀት፣ ማሳወቅ፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 22. | የሚዲያ ተቋማት እና ባለሙያዎች ፖሊሲውን እና የሽግግር ፍትህ ሂደቱን በተመለከተ የሚያዘጋጇቸው ዘገባዎች በሙሉ እውቀት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ለማድረግ - ለሚዲያ ተቋማት አመራሮች፣ ለዜና እና ፕሮዳክሽን ክፍል ዋና ኤዲተሮች፣ ሪፖርተሮች፣ የመንግስት የህዝብ ግንኙነት አመራሮች፣ ለማህበረሰብ ዐቀፍ ሬዲዮ ተወካዮችና ለተመዘገቡ ዩቲዩበሮች ተከታታይ ይዘት-ተኮር ስልጠናዎችን፣ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ መስጠት፣ (6) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ | ምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 23. | የሚዲያ ተቋማት በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ተከታታይነት ያላቸው የራሳቸው ሳምንታዊ ፕሮግራሞች እንዲቀርፁ ማድረግ፣ የተመረጡ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ (በሳምንት አንድ፣ በአመት 52) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ የሚዲያ ካውንስል፣ | ከምእራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 24. | በፖሊሲ ትግበራ ምዕራፍ የተከናወኑ ስራዎችን በምስል (ስፖት) ማቀናበር፣ ለሚዲያ ተቋማት መላክ፣ በሽግግር ፍትህ፣ በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገፆች እና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ማጋራት፣ (26) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሰክሬታሪያት፣ | ከምእራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 25. | የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቶች አሁናዊ ሁኔታን የተመለከቱ ጋዜጣዊ መግለጫዎች በአማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፡<br>ለሚዲያ ተቋማት መላክ፡ በሽግግር ፍትህና በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገፆች እና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ማጋራት፡ (12)<br>ጋዜጣዊ መግለጫ ኮንፈረንስ ማካሄድ (4) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 26. | በሁሉም የሽግግር ፍትህ ሂደት የሰነድ እና ዜና ዝግጅቶች ላይ የሚሰፍር ቋሚ ታግላይን ማዘጋጀት፡ ጥቅም ላይ ማዋል፡ ("የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ስርአት በሀገርና በህዝብ መሪነትና ባለቤትነት እውን ይሆናል") (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 27. | በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ለሚዲያዎች በሚሰጥ ወቅታዊ ጋዜጣዊ መግለጫዎች የሽግግር ፍትሕ ጉዳይ መደበኛ አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፡ ከአመራሮች ጋር ውይይት ማካሄድ፡ ውሳኔ ማሳለፍ፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 28. | የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቶች አሁናዊ ሁኔታን በተመለከተ በኢትዮጵያ ለሚገኙ የውጭ አገራት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፡ ዓለም-አቀፍ ተቋማት እና የልማት አጋሮች መደበኛ የመረጃ ልውውጥ (briefing) መድረኮችን ማዘጋጀት፡ (4) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት ሴክሬታሪያት፡<br>ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| | | | | |

## 9. የህግ ማውጣት/ማሻሻያ ስራዎች

### 9.1. መግቢያ

በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ስርአትን በተሟላ መንገድ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር በርካታ የህግ ማሻሻያ እና አዳዲስ ህጎች የማውጣት ስራዎችን ማከናወን ይጠይቃል። በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ አቅጣጫ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ እና ዋናው ወደፊት የሚደራጁ ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎችን ማውጣት ሲሆን፡ ሁለተኛው የህግ ማእቀፍ የሚያስፈልጋቸውና የአሰራር ስርአት የሚዘረጋላቸው ጉዳዮችን የሚመለከት ነው።

በመሆኑም ፖሊሲውን በሙሉ ሀይል መተግበር እንዲቻል በሰነዱ ላይ የተመላከቱ ጉዳዮችን ለማስፈጸም የሚያስችሉ የህግ ማእቀፎችን ምንነት እና አይነት፡ እንዲሁም የአሰራር ስርአት ሊዘረጋላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በግልጽ መዘርዘር ያስፈልጋል።

### 9.2. አዲስ የህግ ማእቀፍ የሚወጣላቸው/የህግ ማሻሻያ ስራ የሚያስፈልጋቸው ዋና ዋና ርእሰ-ጉዳዮች

በፖሊሲው ላይ የተመላከቱ አዲስ የህግ ማእቀፍ የሚወጣላቸው አሊያም የህግ ማሻሻል ስራን የሚጠይቁ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።

- የዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን የሚደነግግ አዋጅ፡-

- በሀገሪቱ የወንጀል ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎች (በተለይም በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ ሰው ማሰቃየት፣ ሰው መሰወር፣ ጾታዊ ጥቃት እና የተወሰኑ የጦር ወንጀልን) ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማጣጣም አዲስ የሕግ ማዕቀፍ መቅረጽ፣
- ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በማካተት የሚወጣው ህግ ዋና መሰረት የዓለም-አቀፍ የልማድ ህግ (customary international law) እንደመሆኑ መጠን የህጉ ተፈፃሚነት ወሰን ህጉ ከሚጸናበት ቀን በፊት የተፈጸሙ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በሚያቅፍ አግባብ እንዲሆን የሚያስችል የህግ መርህ መመስረት፣

- ክሶችን የመስማት/ውሳኔ የመስጠት ተግባራትን ከሚያከናውነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ልዩ ተቋማዊ አደረጃጀት ጋር በተያያዘ ጉልህ ጥሰቶችን/ወንጀሎችን የማየት የመጀመሪያ፣ የይግባኝ እና የሰበር ዳኝነት ስልጣን፣ የዳኞች መለየት/ማጥራት፣ ማግለል እና ከህላፊነት አነሳስ የሚመለከቱ ጉዳዮችን በአዋጅ መመስረት፣

## 9.3. የህግ ማርቀቅ/ማሻሻያ ስራ የሚከናወንበት አግባብ እና የጊዜ ሰሌዳ

በዚህ ክፍል የህጎች ማርቀቅ ሙሉ ስራን ለማጠናቀቅ የተቀመጠው የጊዜ ማእቀፍ ለህጎቹ መነሻ የሚሆኑ የዳሰሳ ጥናቶች ዝግጅት የሚወስደውን ጊዜ፣ በረቂቅ ህጎቹ ላይ የሚደረጉ ምክክሮችን፣ ረቂቆችን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ልኮ ለማስፀደቅ የሚወስደውን ጊዜ፣ እና ሂደቱ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚቀይበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የአለም-አቀፍ ወንጀሎች አዋጅ፡<br>- የረቂቅ ዝግጅት፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት፣<br>- የረቂቅ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምእራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣<br>ምእራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 2. | የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፡<br>- ነጻና ገለልተኛ ችሎት ከማቋቋም አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን (በዋናነት የልዩ ችሎቱ አደረጃጀት፣ ልዩ ችሎቱ የሚያያቸው ጉዳዮች አይነት ዝርዝር፣ ዳኛ ሆኖ ለመሾም ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ ዳኞችን በተመለከተ ህዝብና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እና አስተያየት የሚሰጡበት ሥርዓት፣ የዳኞች ስብጥር፣ በልዩ ችሎቱ በአማካሪነት እና በአሰልጣኝነት የሚሰሩ ባለሙያዎች፣ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣<br>ከየሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>ፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምእራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣<br>ምእራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የልዩ ችሎቱ ሬጂስትራር፣ የተጎጂዎች ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት፣ የተከላካይ ጠበቆች ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት፣ ዳኞች የሚነሱበት እና የሚተኩበት ሥርዓት ላይ የሚያተኩር)፣<br>- የልዩ ችሎቱን ስልጣንና ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣ | | | |
| | | | | |

## 10. የሽግግር ፍትህ ተቋማት አደረጃጀት

### 10.1. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ስራዎችን የሚያከናውኑ ተቋማት ዝርዝር

የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ እና ዋናው በፖሊሲው ላይ የተቀመጡት ዓላባዎችን የሚተገብሩ ነጻ እና ገለልተኛ ተቋማት ማቋቋም ነው፡፡ በፖሊሲው እሳቤ መሰረት እነዚህን ተቋማት - ተገቢ ስልጣን፣ ሀላፊነት፣ የአሰራር ስርአት እና ተያያዥ ገዝ መርሆችን ባካተተ አግባብ እንዲቋቋሙ ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ረገድ የሚወጡ የሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች በውስጣቸው የተለያዩ ጉዳዮችን ሁሉን-አቀፍ በሆነ መልኩ በማደራጀት የሚወጡ ይሆናል፡፡ ፖሊሲውን በሙሉ ሀይል የሚተገብሩ ተቋማትን ከማደራጀት አንፃር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- **የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራዎች፣**
  - የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራ የሚያከናውን የሽግግር ፍትህ ልዩ አቃቤ ህግ ተቋም ማቋቋሚያ ህግ አዋጅ ዝግጅት እና ተቋማዊ አደረጃጀት አዋጅ፣
  - የወንጀል ተጠያቂነት የስረ-ነገር ወሰን የሚያርፍባቸው ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎችን ሰፋ ካለ ማእዘን በማየት ለመለየት የሚያስችል ግልፅ መስፈርት ዝግጅት፣
  - የወንጀል ተጠያቂነትን የግል ወሰን (personal jursidiction) በተመለከተ በሰብአዊ መብት ጥሰት/ከባድ ወንጀል አፈፃፀም ከፍተኛ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች የሚለዩበት ግልጽ የህግ ሥርዓት ማስቀመጥ፣
  - በሽግግር ፍትህ ሂደት የወንጀል ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ልዩ የምርመራና ክስ ስርዓት፥ የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራ በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችል በሽግግር ፍትህ ሂደት የሚታዩ ወንጀሎችን ልዩ ባህሪ መሰረት ያደረገ የህግ አሰራር ማቆም (በሕገ-መንግስቱ፣ በወንጀል ሕጉ እና በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ ከምርመራ እና ክስ ጋር በተያያዘ የተቀመጡ መርሆዎች እና ድንጋጌዎችን የሚያጠናክር)፣

- በክስ እና ምርመራ ሂደት የሚተገበሩ የሥነ-ሥርዓት እንዲሁም የማስረጃ ህጎች ጾታዊ ጥቃት የፈጸሙ አጥፊዎችን ተጠያቂነት ማረጋገጥ በሚያስችሉ መልኩ መመስረት፣
- በፖሊሲው የተካተቱ ወንጀሎችን በተመለከተ የወንጀል ሙሉ ተጠያቂነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ያለመከሰስ መብት ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የሚያስችል መርህ መመስረት፣
- በሀገር ውስጥ የማይገኙ ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ከሚገኙበት አገር ተላልፈው እንዲሰጡ ለማድረግ የሚያስችል የህግ አሰራር ማቆም፣
- የማበረታቻ ድጋፍ ወይም ሽልማት የሚሰጥበት ስርአት፥ በመደበኛ ምርመራ ሊደረስበት የማይችል ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ አጥፊ ለጠቀመ ወይም ማስረጃ ላቀረበ ሰው የሚሰጥ የማበረታቻ ድጋፍ/ሽልማት አሰራር በህግ ማቆም፣
- ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች ስለሚሰጣቸው የደህንነት ጥበቃና የስነልቦና አገልግሎት ድጋፍ ስርአትን የሚያደራጅ የህግ ማእቀፍ ማውጣት፣

- **የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት፣ የእርቅ፣ ምህረት እና ማካካሻ ስራዎች፣**
    - የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት፣ የእርቅ፣ ምህረት እና ማካካሻ ተግባራትን የሚያከናውን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣
    - እውነት የማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣትና የእርቅ ስራዎች ስረ-ነገር ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ሂደቱ የሚሸፍናቸው አጥፊዎች ወሰን በህግ መደንገግ፣
    - ምህረት በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሚሰጥበትን ዝርዝር አግባብ/መስፈርት እና ምህረት የማይሰጥባቸው የወንጀል አይነቶች/ተሳትፎዎችን በህግ መመስረት፣
    - የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም/ዘላቂ ማካካሻ ስርዓት የህግ ማእቀፍ መመስረት፣
- **የህግና ተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎችን የሚያከናውን ኮሚሽን** ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣

## 10.2. የሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋም ስራ የሚከናወንበት አግባብ እና የጊዜ ሰሌዳ

በዚህ ክፍል ተቋማትን ለማደራጀት የተቀመጠው የጊዜ ማእቀፍ - የየተቋማቱን ማቋቋሚያ ረቂቅ ህግ ለማዘጋጀት የሚወስደውን ጊዜ፣ በረቂቅ ህጎቹ ላይ የሚካሄዱ የህዝብ ምክክሮች፣ እንዲሁም ረቂቆችን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ልኮ ለስማፀደቅ የሚወስደውን ጊዜ፣ እና የተቋማትን ፅህፈት ቤት እና የሰው ኃይል ለማደራጀት የሚያስፈልገውን ጊዜ ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የሽግግር ፍትህ ልዩ አቃቤ ህግ ተቋም ማቋቋሚያ ህግ አዋጅ ዝግጅት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ስራዎች፣<br>- የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን ነጻና ገለልተኛ አድርጎ ከማቋቋም አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን (በዋናነት በተቋሙ አደረጃጀት፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣<br>ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የሃላፊዎች አሿሿም፡ ለሹመት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፡ የዐቃብያነ ሕግ እና መርማሪዎች አሿሿም እና አነሳስ፡ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት የስራ ዘመን፡ የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ ስልጣንና ተግባር፡ የበጀት ነፃነት፡ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት እና ቅንጅታዊ አሰራር፡ በስራ ላይ ያሉ ህጎች ተፈጻሚነት ላይ ያተኮረ)፡<br>- የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን አደረጃጀት፡ ስልጣን፡ ተግባር የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ማዘጋጀት፡<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፡<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፡<br>- የሚተገብር አካልን ማሰልጠን፡<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤት፡ ሰው ኃይል የማደራጀት ስራ፡ | ቤት ጋር በመተባበር፡ | | |
| 2. | የእውነት ማፈላለግ/ማውጣት፡ የእርቅ፡ ምህረት እና ማካካሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፡<br>- የእውነት ማፈላለግ፡ ይፋ ማውጣት፡ እርቅ፡ ምህረት እና ማካካሻ ተግባራትን ነጻነትን፡ ገለልተኛነትን፡ ተቀባይነት እና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ መንገድ ከመተግበር አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን፡ (በዋናነት በተቋሙ አደረጃጀት፡ የሃላፊዎች አሿሿም፡ ለሹመት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፡ የኮሚሽነሮች አሿሿም/አነሳስ፡ የስራ ዘመን፡ የተቋሙ ስልጣንና ተግባር፡ የበጀት ነፃነት፡ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት/ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ያተኮረ)፡<br>- የኮሚሽኑን ስልጣን፡ ተግባራትና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፡<br>- የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም፡ ዘላቂ ማካካሻ ስርዓት አዋጅ ማርቀቅ፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፡<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፡ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፡<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ 3፡ (ታህሳስ - የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | - የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤት እና ሰው ኃይል ማደራጀት ስራ፣ | | | |
| 3. | የህግና ተቋማዊ ማሻሻያ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣<br>- የልየታ፣ ማጥራት እና ማሻሻያ ስራዎችን ነጻነትን፣ ገለልተኛነትን፣ ተቀባይነት እና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ መንገድ ከመተግበር አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ ጥናት/የአውድ ትንታኔ ማከናወን፣<br>- የልየታ፣ ማጥራት እና ማሻሻያ ስርዓትን የሚመራ፣ የኮሚሽኑን ስልጣንና ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማስጸደቅ፣ የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- አዋጁን የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤት እና ሰው ኃይል ማደራጀት ስራ፣ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምእራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## 10.3. የተቋማት አቅም ግንባታ ስራ

ለሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ትግበራ የሚቋቋሙ ተቋማትን በተመለከተ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በጥንቃቄ ማቀድ እና መተግበር ያስፈልጋል። የአቅም ግንባታ ስራዎቹ በአጭር እና በረጅም ጊዜ እቅድ ውስጥ የሚከናወኑ ይሆናል። በዋናነትም ስራዎቹ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገው ይከናወናሉ።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አዲስ የሚቋቋሙ ሁሉም የሽግግር ፍትህ ተቋማት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን በሙሉ አቅማቸዉ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል የሚከተሉት የአቅም ግንባታ ስዎች ይሰራሉ<br>- አዲስ ለሚቋቋሙ ተቋማት አመራሮች በፖሊሲው እና ትግበራ ሂደቶች፣ በተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች ይዘት፣ በሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ሚና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን መስጠት፣ (3)<br>- አዲስ ለተቋቋሙ ተቋማት ባለሙያዎች በሽግግር ተመሳሳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን መስጠት፣ (3) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | - የሽግግር ፍትህ ተቋማትን በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና በቴክኒክ ሊደግፉ የሚችሉ የልማት አጋሮች እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በዝርዝር መለየት፡ የባለድርሻ አካላት ልየታ (Stakeholdes Mapping) ማዘጋጀት፡ (1)<br>- በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የልማት አጋሮች እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሚኖራቸው ሚና ላይ ዎርክሾፕ ማዘጋጀት፡ (2) | | | |
| 2. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ዝርዝር የአቅም ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ፥<br>- የተቋሙ አመራሮች፡ ባለሙያዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በዓለም-አቀፍ ወንጀሎች የምርመራ እና ክስ ቴክኒካዊ አሰራር ላይ የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው አማካሪዎች መቅጠር፡ የአማካሪዎች ምልመላ/ሚና ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (2)<br>- በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ፡ በዓለም አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ እና ክስ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ቴክኒካዊ ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት ወይም ባለሙያዎችን መለየት፡ ስልጠናዎች መስጠት፡ (4)<br>- በተቋሙ ውስጥ በሰው ኃይል እና በግብዓት የተደራጀ የትምህርትና ስልጠና ማዕከል ማደራጀት፡ (1)<br>- በተቋሙ ውስጥ በአለም አቀፍ ወንጀሎች ይዘት፡ ምርምራ/ክስ ሂደት፡ እና ክስ ጉዳዮች አስተዳደር (Case Management) እና ተጎጂ-ተኮር አሰራር ላይ የስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፡<br>- የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ለማድረግ የሚያስችሉ የወንጀል ምርመራ፡ ክስ እና ማስረጃ አስተዳደር ስርዓት ማበልጸግ፡<br>- የተቋሙ አመራር እና የተመረጡ አቃብያኔ ህጎች በወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራ ሂደት ስኬታማ ታሪክ ባላቸው የአፍሪካ እና ሌሎች አገራት የስራ ጉብኝት እና የልምድ ልውውጥ መርሀ-ግብሮችን ማመቻቸት፡ (3)<br>- የመብት ጥሰት ሰለባዎችን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ባለበት ሆኖ የወንጀል ድርጊት ጥቆማ እና ማስረጃ የሚያቀርቡበት ነጻ የስልክ ጥሪ ማዕከል፡ ድህረ-ገፅ ማደራጀት፡ (1)<br>- የተቋሙን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎች እና | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦች እና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፣<br>- የተቋሙን የስራ ስፋት እና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፣ | | | |
| 3. | የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎት አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፡-<br>- የችሎት አመራሮች፣ ዳኞች፣ ሬጅስትራሮች፣ ተከላካይ ጠበቆች እና የተጎጂዎች ድጋፍ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ባለሙያዎችን በዓለም አቀፍ ወንጀሎች የክስ እና ክርክር መስማት፣ ችሎት አመራር፣ ውሳኔ አሰጣጥ እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣ቅጥር ለማካሄድ፣ (2)<br>- ከላይ ለተመለከቱ አመራሮች በሽግግር ፍትሕ ሂደት የዓለም አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ፣ ክስና ክርክር፣ ችሎት አመራር፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ተጎጂ-ተኮር የፍርድ ሂደት እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይ እና አውድ-ተኮር የሰልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ ስልጠናዎች መስጠት፣ (5)<br>- የችሎት አመራሮች እና የተመረጡ ዳኞች በስኬታማነት በሚጠቀሱ የአፍሪካ እና ሌሎች አገራት፣ የሩዋንዳ የወንጀል ፍርድ ቤት (ቀድሞ ባለሙያዎች)፣ እና አለማቀፍ ፍርድ ቤት (ICC) ጉብኝት በማድረግ በሽግግር ፍትሕ የወንጀል ክስ እና ክርክር ሂደት፣ የችሎት አመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ ጉዳይ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፣ (3)<br>- የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎቶች እና እንደአስፈላጊነቱ በየክልሎች የሚደራጁ ምድብ ችሎቶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት ተደግፈው እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችሉ ግብቶችን ማሟላት፣ ለዚህ የሚያስፈልግ የተፈላጊ መሰረተ-ልማት ቴክኒካል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣<br>- የችሎቱን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፣ መረጃዎችን፣ የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦች እና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፣<br>- የተቋሙን የስራ ስፋት እና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፣ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣<br>ምእራፍ 3፣ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4. | የእውነት ማፈላለግ፣ ምህረት እና ማካካሻ ኮሚሽን አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት የአቅም ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ፡<br>- በጉልህ አለም-አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ እና ክስ፣ በአማራጭ ግጭት መፍቻ መንገዶች፣ የእውነት ማፈላለግ እና ይፋ ማውጣት ስርአት፣ በምህረት እና ይቅርታ አስተዳደር እና ተመራጭ የማካካሻ ስራዎች አካሄድ ላይ ተቋሙን እና ሀላፊዎቹን የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣ ቅጥር ማካሄድ፡ (2)<br>- በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይ እና አውድ-ተኮር የሰልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ ስልጠናዎች መስጠት፣ (5)<br>- ኮምሽነሮች እና የተመረጡ የተቋሙ ባለሙያዎች በስኬታማነት በሚጠቀሱ የአፍሪካ እና ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፡ (3)<br>- ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር የተያያዙ የታሪክ መዝገቦችን፣ የተጎጂዎችን ምስክርነት ቃል እና ሌሎች ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ እና ለማቀየት የሚያስችል የኮሚሽን አርካይብ እንዲደራጅ ቴክኒካል መዘርዝር ማውጣት፣ መሰረተ-ልማቱን ማዘጋጀት፣ (1)<br>- የኮሚሽኑን ስራዎች ለማዘመንና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፣ መረጃዎችና የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦችንና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቀየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፣<br>- መረጃዎችን፣ የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦች፣ ማሳያዎች እና ሌሎች ሰነዶችን አሰብስቦ ለማቀየት እና ለትውልድ ለማሰቀመጥ የሚያስችል ሙዝየም ማደራጀት፣<br>- የተቋሙን የስራ ስፋት እና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፣ | ኮሚሽን፣<br>የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 3፣ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 5. | የተቋማዊ ማሻሻያ ኮሚሽን አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፡<br>- በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የሚከናወኑ ተቋማዊ ማሻሻያ ጉዳዮች ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ እና አካሄድ ላይ ተቋሙን እና ሀላፊዎቹን የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣ ቅጥር ማካሄድ፡ (1)<br>- በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይ | ኮሚሽን፣<br>የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 4፣ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | እና አውድ-ተኮር የሰልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ ስልጠናዎች መስጠት፣ (5)<br>- ኮምሽነሮች እና የተመረጡ የተቋሙ ባለሙያዎች በስኬታማነት በሚጠቀሱ የአፍሪካ እና ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፣ (3)<br>- የኮሚሽኑን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፣ መረጃዎችንና የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦችንና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቀየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፣<br>- የተቋሙን የስራ ሰፋት እና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፣ | | | |
| | | | | |

## 11. በሽግግር ፍትህ ትግበራ የክልሎችን ተሳትፎ እና ሀላፊነት ለመለየት/ለማሳለጥ የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች

### 11.1. መግቢያ

የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊያሳካው ከሚሻው ዓላማ አንፃር - በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሚሳለጥ አንድ ወጥ የሽግግር ፍትህ ስርአት ትግበራ ሊኖር ይገባል። እንዲያም ሆኖ የሽግግር ፍትህ ስራ እንዲፈታቸው ከሚታሰቡ ጉዳዮች ይዘት፣ ብዛት፣ አካባቢያዊ ስርጭት እና ውስብስብነት አንፃር ክልሎች ግልፅ ሀላፊነቶችን በመሸከም በትግበራ ምእራፎች እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ነው።

በመሆኑም የሽግግር ፍትህ ተቋማት ለመመስረት የሚወጡ ህጎች የሚያስቀምጡት አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ - ክልሎች በአገራዊ እና አካባቢያዊ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ አውድ የሚኖራቸውን ሀላፊነት በቅልጥፍና እና ውጤታማነት እንዲወጡ ከማድረግ አንፃር ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ።

### 11.2. ክልሎች በሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ የሚኖራቸው ሀላፊነት

በፌዴራል የሽግግር ፍትህ ተቋማት የስረ-ነገር ስልጣን ማእቀፍ ስር የሚወድቁ ጉዳዮች ቴክኒካል ዝርዝር፣ እና በዚህ ማእቀፍ ክልሎች ለፌዴራል ተቋማት የሚሰጡት ድጋፍ እና ትብብር ይዘትን የሚያመላክት ዝርዝር ሰነድ ይዘጋጃል።[2]

- ይህ ሰነድ የፌዴራል ተቋማት የስረ-ነገር ስልጣን ቢኖራቸውም በተለያዩ ምክንያቶች የማይተገብሯቸው የሽግግር ፍትህ ጉዳዮችን የሚያካትት ይሆናል።
- በተጨማሪም ሰነዱ ከአገር-አቀፍ የሽግግር ፍትህ መሰረታዊ መርሆች ጋር በተናበበ አግባብ በክልሎች ሙሉ ባለቤትነት፣ ሀላፊነት - ገለልተኛ እና ፍትሀዊ አሰራር በመዘርጋት የሚከናወኑ ክልል-አቀፍ የእውነት ማፈላለግ፣ የእርቅ እና ማካካሻ የሽግግር ፍትህ ስራዎችን ዝርዝር የሚያመላክት ቴክኒካል ዝርዝር ይይዛል።

[2] የክልሎች ተሳትፎ ዝርዝርን በተመለከተ - የሚዘረጋው ስርአት ትኩረት በሚከተሉት ተግባራት ላይ ሊሆን ይችላል፦ ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችን መለየት/መምረጥ፣ ተጎጂዎችን መለየት፣ የማካካሻ ስራን በገንዘብ መደገፍ፣ ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋም፣ የጥሰት ታሪክን ለማከም የሚረዱ ማስታወሻዎችን ማዘጋጀት፣ ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ መሳካት የሚፈለጉ ማስረጃዎችን ማቅረብ፣ የውይይት ጊዜና ቦታዎች ማዘጋጀት፣ ሎጂስቲክስን ማሳለጥ፣ ጥፋተኞችን ሪፖርት ማድረግ/ለፍርድ ማቅረብ፣ የሚያስተዳድሩት ህዝብ በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ላይ አመኔታ እንዲኖረው የግንዛቤ መድረኮችን ማዘጋጀት፣ የህዝቦች አብሮነት እና ግንኙነት የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት፣ የክልሉን ህዝብ ተሳታፊነት ማረጋገጥ፣ ለተቋማዊ ሪፎርም ዝግጁ መሆን፣ የጸጥታ እገዛ ማድረግ።

ለዚህ አላማ በሽግግር ፍትህ ሂደት ክልሎች የሚጠበቅባቸውን ሀላፊነት ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲወጡ ለማስቻል ክልሎች እና የአገራዊው የሽግግር ፍትህ ስራዎች ዘላቂ አደረጃጀት በጋራ በመሆን ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአት ይቀርፃሉ፡፡

ከአገራዊ የሽግግር ፍትህ ስራ ቋሚ አደረጃጀት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት በየክልሎቹ ታችኛው መዋቅር የሚገኝ ህዝብ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱን በተመለከተ ተገቢ ግንዛቤ እና አመኔታ እንዲኖረው ለማድረግ፣ ተሳታፊነቱን እና የህዝቦችን ሰላም ለማጎልበት፣ እና በጉዳዩ ላይ የአላማ አንድነት ለማጠናከር የሚያስችሉ ተከታታይ እና የተደራጁ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮች ዝግጅት እና ግንዛቤ ፈጠራ ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡

ሁሉን-አቀፍ በሆነ አገራዊ የማካካሻ ስርአት ማእቀፍ ክልሎች የሚተገብሯቸው የማካካሻ ስራዎች (ካሳ፣ ማገገሚያ፣ ወደ ነበሩበት መመለስ፣ እርካታ፣[3] እና ያለመድገም ዋስትና) አይነት፣ ሂደት፣ አተገባበር እና አመላካች የጊዜ ሰሌዳን የሚመራ ማንዋል ይዘጋጃል፣ ይተገበራል፡፡

በክልሎች ደረጃ ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ያስቻሉ የህግ ማዕቀፎች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ውስን ተቋማትን በተገቢ መልክ ለመለየት፣ ለማጥራት እና ለመለወጥ የሚረዳ ስትራቴጂ/አደረጃጀት ይዘጋጃል፣ ተቋማትን የመገንባት ስራ ይከናወናል፡፡

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | በሽግግር ፍትህ አተገባበር የክልሎችን ተሳትፎ እና ሀላፊነት ዝርዝር የሚያስቀምጥ ሁሉን-አቀፍ መሪ ሰነድ (Comprehensive Guiding Document) ማዘጋጀት፣ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>ከክልሎች ጋር የሚፈጥረው ቅንጅታዊ አሰራር፣ | ምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 2. | በክልሎች ታችኛው መዋቅር በሚገኝ ህዝብ ላይ ያተኮሩ ተከታታይ እና የተደራጁ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮች ዝግጅት እና የግንዛቤ መፍጠሪያ ስራዎች ማከናወን፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>ከክልሎች እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የሚፈጥረው ቅንጅታዊ አሰራር፣ | ምእራፍ 1 (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 3. | በክልሎች ደረጃ ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ያስቻሉ የህግ ማዕቀፎች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ውስን ተቋማትን በተገቢ መልክ ለመለየት፣ ለማጥራት እና ለመለወጥ የሚረዳ ቴክኒካል ሰነድ ማዘጋጀት፣ የተቋማዊ ሪፎርም መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፣ ትግበራ መጀመር፣ | የክልል ፍትህ ቢሮዎች፣ መስተዳድሮች፣ | ምእራፍ 4፣ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፣ | |
| | | | | |

## 11.3. የባህላዊ ፍትህ ስርዓቶች ሚና

ኢትዮጵያ በርካታ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ያሏቸው ማህረሰቦች አገር እንደመሆኗ መጠን እነዚህ ሥርዓቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል፡፡

---

[3] የትግበራ ስራዎቹ የጥሰቶችን ሙሉ ሀቅ ማፈላለግ/ይፋ ማውጣት፣ እንደ መንግስት ለተፈጸሙ በደሎች በተለያየ መንገድ በይፋ ይቅርታ መጠየቅ (ለምሳሌ ለተለዩ ተጎጂዎች የይቅርታ ደብዳቤ መጻፍ)፣ የመታሰቢያ/ማስታወሻ ክንዋኔዎች ማዘጋጀት/ሰያሚዎች መስጠት ያካትታል፡፡

ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በአገራዊ እና አካባቢያዊ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ አውድ የሚኖራቸውን ሀላፊነት እንዲወጡ ከማድረግ አንፃር የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ።

- ክልሎች በአገር-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ስራ የሚሳተፉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶችን በሚቀመጡ ግልፅ መመዘኛዎች መሰረት ይለያሉ፣ ያሳውቃሉ። ለዚህ የሚሆን ዝርዝር ቴክኒካል ማንዋል ይዘጋጃል።
    - ሰነዱ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በሽግግር ፍትህ ሂደት የፌዴራል መንግስትን ሆነ ክልሎችን በማገዝ እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት በእውነት ማፈላለግ፣ በእርቅ፣ ተጠያቂዎች ለፍትህ እንዲቀርቡ በመርዳት፣ እና በማካካሻ ስራዎች የሚኖራቸውን ሚና፣ የሚለዩበት መመዘኛ፣
    - እንዲሁም ተቋማቱ ሀላፊነትና እውቅና የሚያገኙበትን አግባብ፣ ገለልተኛነታቸውን፣ ነጻነታቸውን እና ተዓማኒነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተጠባቂ አነስተኛ ማሻሻያዎችን፣ እና ጉዳዮችን የማስተናገድ ተቋማዊ አቅማቸውን ተጎጂ-ተኮር በሆነ አግባብ ማከናወን እንዲችሉ የሚያግዙ የአደረጃጀት/መዋቅር እና ስልጠና ስራዎች የሚከናወኑበትን አግባብ የሚዘረዝር ይሆናል።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | በሽግግር ፍትህ ስራ የሚሳተፉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች መለያ እና ማሳወቂያ አሰራር፣ የሚኖራቸው ሀላፊነት፣ እና ስራቸውን የሚያከናውኑበትን አግባብ የሚዘረዝር ቴክኒካል ማንዋል ዝግጅት፣ | ክልሎች እና ከባቢያዊ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ጋር የሚፈጥሩት ትብብር፣ | ምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 2. | የተመረጡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ተቋማትን አቅም የመገንባት ስራ፣ | ክልሎች እና ከባቢያዊ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ጋር የሚፈጥሩት ትብብር፣ | ምእራፍ 4፣ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፣ | |

## 12. ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በትግበራ ሂደት የሚኖራቸውን ሚና ለመለየት/ለማስፈፀም የሚከናወኑ ተግባራት

የሽግግር ፍትህ የትግበራ ሂደት ልዩ ትኩረት ለሚሹ እና ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለሴቶች፣ ለህጻናት፣ ለወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን እና ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ልዩ ፍላጎት እና ጥቅም ትኩረት በሚሰጥ አግባብ ሊከናወን ይገባል።

በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተሳትፎ እና ጥበቃ ከማረጋገጥ አንፃር የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ዝርዝር ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣ መተግበር፣ | የተቋማት ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ እና አጋሮች ጋር በመቀናጀት፣ | ምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 2. | የሽግግር ፍትህ ስርአት ስራዎች የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎችን ድምፅ እና ተሳትፎ ባረጋገጠ አግባብ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መደበኛ የክትትል ስርአት | የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቅንጅት፣ | ከምእራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | (Monitoring Mechanism) ማዘጋጀት፣ መደበኛ የክትትል ስራዎች ማከናወን (2)፡ | | | |
| 3. | የሽግግር ፍትህ ተቋማት አደረጃጀት የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችል የስራ ክፍል እንዲኖራቸው ማድረግ፡ | የተቋማት ጊዜያዊ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 4. | የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መብቶች፣ ደህንነት፣ ፍትህ እና መሰረታዊ ፍላጎቶችን ከማሟላት አንፃር አስቸኳይ እና ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የሚያስችል የድርጊት መርሃ-ግብር መንደፍ፣ መተግበር፡ | የሰላም ሚኒስቴር፡ የአደጋ መከላከል እና ዝግጁነት ኮሚሽን፡ ከተቋማት ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ጋር በመቀናጀት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## 13. ለፆታ ጥቃት ሰለባዎች ልዩ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት የሚተገበሩ ተጨማሪ እርምጃዎች

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የወንጀል ተጠያቂነት ስራዎች ሂደት ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ምቹ እና አሳታፊ ማድረግ፡<br>ደህን የሚያግዝ ራሱን የቻለ ንኡስ መዋቅር ማደራጀት፡ | የተቋማት ጊዜያዊ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከኮሚሽኖች እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 2. | በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የስነልቦና፣ የምክር እና የህክምና ድጋፍ የሚቀርብበት ሁሉን-አቀፍ ዘላቂ አደረጃጀት/ስርአት መመስረት፡<br>የፆታ ጥቃት ሰለባ አገልግሎት መሰረተ-ልማቶችን (አንድ ማእከሎች፣ ማገገሚያ ተቋማት) ማጠናከር፡<br>መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፣ መተግበር፡ | የተቋማት ጊዜያዊ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከኮሚሽኖች፣ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 3. | በአጭር ጊዜ በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች (በተወሰኑ ቡድኖች ላይ ያተኮረ) የስነልቦና፣ ምክር እና ህክምና ድጋፍ የሚቀርብበት ጊዜያዊ አደረጃጀት መመስረት፣ ማጠናከር፡ ስራዎችን መተግበር፡ | የተቋማት ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከኮሚሽኖች፣ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 4. | በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ኢኮኖሚያዊ (ራስ-አገዝ) አገልግሎት የሚቀርብበት አደረጃጀት መመስረት፣ ማጠናከር፡<br>መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፣ መተግበር፡ | የተቋማት ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከኮሚሽኖች፣ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምእራፍ 5፡ (ሰኔ-ነሃሴ 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |

## 14. የሽግግር ፍትህ ትግበራን የሚመለከቱ ሀገራዊ መረጃዎች የሚያዙበት፣ የሚደራጁበት እና ተደራሽ የሚሆኑበት የመረጃ ቋት ስርዓት

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | ለትግበራ የሚያስፈልግ በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የመረጃ መሰረተ-ልማት ግንባታ<br>ሀ) ድህረ-ገፅ እና ማህበራዊ ሚዲያ፡<br>- የሽግግር ፍትሕ አገር-አቀፍ ስራዎችን ሂደት፡ ረቂቆች፡ ቃለ-ጉባዔዎች፡ የምክክር ሂደቱ የምስል እና የድምጽ ሪከርዶች፡ ዋና ዋና ሰነዶች፡ ዘገባዎች እና ወቅታዊ ሪፖርቶችን የሚይዝ ድህረ-ገፅ ስራ ማጠናቀቅ፡ ከአልሚው መረከብ፡<br>- ለዚሁ ዓላማ ከፍተኛ አቅም ያለው ሰርቨር ኪራይ መፈጸም፡<br>- ድህረ-ገፁን እና ሌሎች ለሽግግር ፍትህ ዓላማ የሚከፈቱ የመረጃ ማከማቻ እና ማጋሪያ ዘዴዎችን የሚያስተዳድር፡ በየወቅቱ በአዳዲስ መረጃዎች የሚያደራጅ የሚከታተል፡ ከፍተኛ ብቃት ያለው ቋሚ የዘርፍ ባለሙያ መቅጠር፡ መመደብ፡<br>- ተመሳሳይ መረጃዎችን በተመጠነ አግባብ በፌስቡክ እና ትዊተር ገፆች ላይ ማስፈር፡<br>- የሽግግር ፍትህ ሂደት ዋና ዋና መረጃዎችን በማእከላዊነት የሚይዝ ትልቅ አቅም ያለው መጠባበቂያ የውጭ ቋት (external database/ backup drive) ማዘጋጀት፡<br>ለ) አርካይቭ<br>- የሽግግር ፍትህ ስራ ሂደቶችን የሚመለከቱ የተመረጡ በወረቀት የተዘጋጁ መሰረታዊ ሰነዶች ሚስጥራዊነት እና ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ማእከላዊ የአርካይቭ ስርአት ማደራጀት፡ ለዚህ የሚያገለግሉ ፅህፈት-ቤትና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፡<br>ሐ) ሙዚየም<br>- የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን ዝግጅት ሂደት እና የትግበራ ስራዎችን በተሟላ መልኩ የሚገልፅ በየጊዜውም እየተሟላ የሚሄድ ማሳያ (ሙዝየም) ሴክሬታሪያቱ በሚገኝበት የፍትሕ ሚኒስቴር ህንፃ ውስጥ እንዲደራጅ ማድረግ፡ | የተቋማት ጊዜያዊ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## አባሪ 1: የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል አጠቃላይ እቅድ (Sequenced Implementation – Master-Deck)

| | የሚከናወኑ ተግባራት | ፈፃሚ | የጊዜ ሰሌዳ |
|---|---|---|---|
| 1. | 'የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ' መመስረት | ፍትሕ ሚኒስቴር | ምእራፍ 1: (ሰኔ 15 2016 ዓ.ም) |
| 2. | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ መደበኛ ስብሰባዎች ማካሄድ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት | ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ መድረክ ከተመሰረተ በኋላ (ከሰኔ 2016-ህዳር 2017 ዓ.ም፡ በየሶስት ወር) |
| 3. | 'የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ' መመስረት | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2: ጥቅምት 15 2017 ዓ.ም (ቢያንስ ከቋሚ የሽግግር ፍትህ ተቋማት ውስጥ አንዱ ወደስራ በገባ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ) |
| 4. | የሽግግር ፍትህ ስራዎች በተመለከተ የጋራ ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 5. | መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎች ማካሄድ (4) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2-5: መስከረም-ነሐሴ 2017 ዓ.ም |
| 6. | የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መደበኛ የመስክ ክትትል ስራ (4) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2-5: (መስከረም-ነሐሴ 2017 ዓ.ም) |
| 7. | በሽግግር ፍትህ ተቋማት መካከል ተመጋጋቢ፡ ተደጋጋፊ እና የተቀናጀ የስራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል አሰራር (ገላጭ ሰነድ) ዝግጅት፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1: (ሐምሌ 15 2016 ዓ.ም) |
| 8. | የሽግግር ፍትህ ስራዎች በአገር-አቀፍ ደረጃ ከሚተገበሩ ሌሎች ተዛማጅ የሪፎርምና ስራዎች ጋር የሚኖራቸውን መስተጋብር የሚተነትን፡ ቀጣይ ሂደቶችን የሚመራ ገላጭ ሰነድ ዝግጅት፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1: (ሐምሌ 15 2016 ዓ.ም) |
| 9. | የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ/ትግበራ ሂደቶችን አጠቃላይ ስእል የሚሰጥ መሰረታዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ በተለያዩ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፡ (1)<br>በህትመት እና በድህረ-ገፆች ማሰራጨት፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 10. | የህዝብ ተሳትፎ ለሽግግር ፍትህ ውጤታማነት ያለውን ሚና የሚያሳይ በህዝብ አስተያየት ላይ የተመሰረተ የቲቪ ፕሮግራም ማዘጋጀት፡ ማስተላለፍ፡ (12) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 11. | በሽግግር ፍትህ አላማ እና ግቦች ላይ የሀገሪቱ ርዕሰ-ብሄር አጭር መልዕክት ተቀርጾ በዋና ዋና ቋንቋዎች በሁሉም ሚዲያዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፡ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡<br>የፕሬዚደንት ጽህፈት ቤት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12. | በሽግግር ፍትህ አላማ/ግቦች ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ መልዕክት ተቀርጾ በዋና ዋና ቋንቋዎች በሁሉም ሚዲያዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፡ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 13. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ ምዕራፍ ክልሎችና ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች የሚኖራቸውን ሚና የሚገልፅ ዘጋቢ ቪዲዮ ዶክመንታሪ ማዘጋጀት፡ ማሰራጨት፡ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 14. | የእምነት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲን በመተግበር ሂደት በሚኖራቸው ሚና ዙሪያ ተከታታይ አገር አቀፍ የፓናል ውይይቶችን ማካሄድ፡ (3) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ የሀይማኖት ተቋማት ምክር ቤት፡ የክልል መስተዳድሮች፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 15. | ለፌዴራል እና ክልል መንግስት ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ለክልል ምክር ቤት አባላት የፖሊሲውን ይዘት እና የትግበራ ሂደትን በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (14) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከተቋማቱ ጋር በመተባበር | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 16. | በሁሉም ክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ለሚገኙ የዞንና የወረዳ ሀላፊዎች የፖሊሲውን ይዘት/የትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (28) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከተቋማቱ ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 17. | በአዲስ አበባ/በክልል በሰብዓዊ መብት፡ ግጭት አፈታት፡ የሕግ የበላይነትና ፍትህ ጉዳዮች ላይ ለሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ (awareness, briefing) መድረኮች ማዘጋጀት፡ (10) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ ሶስት (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ |
| 18. | ለፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች የፖሊሲው ይዘት እና ትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (2) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 19. | በሀገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበረሰብ እና ከፍተኛ አመራር የፖሊሲ ይዘት/ትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (10) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 20. | ለዳያስፖራ ማህበረሰብ ተወካዮች የፖሊሲ ይዘት እና የትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (በአውሮፓ፡ አሜሪካ፡ በአረብ ሀገራት፡ ውስን የአፍሪካ አገራት) (5) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከዳያስፖራ ኮሚሽን እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ከምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |
| 21. | በሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆች እና ሌሎች ህጎች ላይ ህዝብ ዝርዝር አስተያየት የሚሰጥበት ከመደበኛው አሰራር የተለየ አገር-አቀፍ የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት፡ (ለአንድ ረቂቅ ህግ 4 አገር-አቀፍ መድረኮች) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 22. | የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱን፡ የህዝብ ምክክርና | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት | ምእራፍ 1፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ግብአት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት፣ እና የፖሊሲውን አማርኛ እና እንግሊዝኛ ቅጂ በህትመት እና በድህረ-ገፆች ማሰራጨት፣ | ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ | (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 23. | የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን ትግርኛ፣ ኦሮምኛ፣ አፋርኛ፣ ሲዳምኛ፣ ጉራግኛ እና ሶማሊኛን ጨምሮ ቢያንስ በአስር አገራዊ ቋንቋዎች መተርጎም፣ ቅጂውን በህትመት እና በማህበራዊ ገጾች እና ድህረ-ገፆች ተደራሽ ማድረግ፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ከየክልሎቹ ፍትህ ቢሮዎች ጋር በመተባበር፣ | ምእራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 24. | የሽግግር ፍትህ ሂደትን የሚመለከቱ ትምህርቶችን/መልዕክቶችን የያዙ አጫጭር ተከታታይ ዘጋቢ ቪዲዮዎችን የሚያዘጋጅ የዘርፉ ባለሙያ መቅጠር፣ ማስማራት፣ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 25. | በስኬታማ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት ያለፉ አገራት ተሞክሮን የሚያሳዩ ታሪካዊ እና ምስላዊ ቅንብር ማዘጋጀት፣ ማሰራጨት፣ (2) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 26. | የሽግግር ፍትሕን የተለያዩ ጉዳዮችን የተመለከቱ ድራማ እና ካርቱን አጫጭር ቪዲዮዎች ማዘጋጀት፣ ማሰራጨት፣ (5) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ከምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፣ |
| 27. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች (ተጎጂዎች፣ የፆታዊ ጥቃት ሰለባዎች፣ ተፈናቃዮች፣ አካል ጉዳተኞች) የሚኖራቸውን ሚና የሚገልፅ ዘጋቢ ቪዲዮ ዶክመንታሪ ማዘጋጀት፣ ልዩ ሁኔታቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ማደራጀት፣ ማሰራጨት፣ (1) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 28. | ለሚዲያ ተቋማት የሚሰጡ መረጃዎች አይነት፣ መረጃ ስለሚሰጥበት ጊዜ/አግባብ፥ የመረጃ እና የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት፣ መረጃ ስለሚሰጠው አካል፥ እና ከሚዲያ ተቋማት ጋር የሚኖር መደበኛ ግንኙነትን የሚገዛ ሁሉን-አቀፍ የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣ ስራ ላይ ማዋል፥ (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 29. | ከሚዲያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በመደበኛነት ምላሽ የሚሰጥ ባለሙያ ማዘጋጀት፣ አከራካሪ እና የብዙሀኑ ሚዲያ ጥያቄ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አንድ ወጥ ምላሽ ማዘጋጀት፣ ማሳወቅ፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 30. | የሚዲያ ተቋማት እና ባለሙያዎች ፖሊሲውን እና የሽግግር ፍትህ ሂደቱን በተመለከተ የሚያዘጋጁቸው ዘገባዎች በሙሉ እውቀት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ለማድረግ - ለሚዲያ ተቋማት አመራሮች፣ ለዜና እና ፕሮዳክሽን ክፍል ዋና ኤዲተሮች፣ ሪፖርተሮች፣ የመንግስት የህዝብ ግንኙነት አመራሮች፣ ለማህበረሰብ ዐቀፍ ሬዲዮ ተወካዮችና ለተመዘገቡ ዩቲዩበሮች ተከታታይ ይዘት-ተኮር ስልጠናዎችን፣ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ መስጠት፣ (6) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ | ምእራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 31. | የሚዲያ ተቋማት በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ተከታታይነት ያላቸው የራሳቸው ሳምንታዊ ፕሮግራሞች እንዲቀርፁ ማድረግ፣ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የተመረጡ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፡ (በሳምንት አንድ፡ በአመት 52) | የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡<br>የሚዲያ ካውንስል፡ | |
| 32. | በፖሊሲ ትግበራ ምዕራፍ የተከናወኑ ስራዎችን በምስል (ስፖት) ማቀናበር፡ ለሚዲያ ተቋማት መላክ፡ በሽግግር ፍትህ፡ በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገፆች እና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ማጋራት፡ (26) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሰክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 33. | የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቶች አሁናዊ ሁኔታን የተመለከቱ ጋዜጣዊ መግለጫዎች በአማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፡<br>ለሚዲያ ተቋማት መላክ፡ በሽግግር ፍትህና በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገፆች እና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ማጋራት፡ (12)<br>ጋዜጣዊ መግለጫ ኮንፈረንስ ማካሄድ (4) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |
| 34. | በሁሉም የሽግግር ፍትህ ሂደት የሰነድ እና ዜና ዝግጅቶች ላይ የሚሰፍር ቋሚ ታግላይን ማዘጋጀት፡ ጥቅም ላይ ማዋል፡ ("የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ስርአት በሀገርና በህዝብ መሪነትና ባለቤትነት እውን ይሆናል") (1) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 35. | በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ለሚዲያዎች በሚሰጥ ወቅታዊ ጋዜጣዊ መግለጫዎች የሽግግር ፍትሕ ጉዳይ መደበኛ አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፡ ከአመራሮች ጋር ውይይት ማካሄድ፡ ውሳኔ ማሳለፍ፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 36. | የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቶች አሁናዊ ሁኔታን በተመለከተ በኢትዮጵያ ለሚገኙ የውጭ አገራት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፡ ዓለም-አቀፍ ተቋማት እና የልማት አጋሮች መደበኛ የመረጃ ልውውጥ (briefing) መድረኮችን ማዘጋጀት፡ (4) | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር ስርአት ሴክሬታሪያት፡<br>ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |
| 37. | የአለም-አቀፍ ወንጀሎች አዋጅ፡<br>- የረቂቅ ዝግጅት፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት፡<br>- የረቂቅ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፡<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፡<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፡<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 38. | የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፡<br>- ነጻና ገለልተኛ ችሎት ከማቋቋም አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን (በዋናነት የልዩ ችሎቱ አደረጃጀት፡ ልዩ ችሎቱ የሚያያቸው ጉዳዮች አይነት ዝርዝር፡ ዳኛ ሆኖ ለመሾም ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፡ የዳኞች ሹመትን በተመለከተ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡<br>ከሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ፍትህ ሚኒስቴር፡<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ህዝብና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እና አስተያየት የሚሰጡበት ሥርዓት፣ የዳኞች ስብጥር፣ በልዩ ችሎቱ በአማካሪነት እና በአሰልጣኝነት የሚሰሩ ባለሙያዎች፣ የልዩ ችሎቱ ሬጂስትራር፣ የተጎጂዎች ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት፣ የተከላካይ ጠበቆች ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት፣ እና ዳኞች የሚነሱበት እና የሚተኩበት ሥርዓት ላይ የሚያተኩር)፡<br>- የልዩ ችሎቱን ስልጣንና ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነግግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣ | | |
| 39. | የሽግግር ፍትህ ልዩ አቃቤ ህግ ተቋም ማቋቋሚያ ህግ አዋጅ ዝግጅት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ስራዎች፣<br>- የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን ነጻና ገለልተኛ አድርጎ ከማቋቋም አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን (በዋናነት በተቋሙ አደረጃጀት፣ የሃላፊዎች አሿሿም፣ ለሹመት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ የዐቃብያነ ሕግ እና መርማሪዎች አሿሿም እና አነሳስ፣ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት የስራ ዘመን፣ የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ ስልጣንና ተግባር፣ የበጀት ነፃነት፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት እና ቅንጅታዊ አሰራር፣ በስራ ላይ ያሉ ህጎች ተፈጻሚነት ላይ ያተኮረ)፡<br>- የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን አደረጃጀት፣ ስልጣን፣ ተግባር የሚደነግግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ማዘጋጀት፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብር አካልን ማሰልጠን፣<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤት፣ ሰው ኃይል የማደራጀት ስራ፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ/ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምእራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 40. | የእውነት ማፈላለግ/ማውጣት፣ የእርቅ፣ ምህረት እና ማካካሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተቋማዊ አደረጃጀት፡<br>- የእውነት ማፈላለግ፡ ይፋ ማውጣት፡ እርቅ፡ ምህረት እና ማካካሻ ተግባራትን ነጻነትን፡ ገለልተኛነትን፡ ተቀባይነት እና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ መንገድ ከመተግበር አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን፡ (በዋናነት በተቋሙ አደረጃጀት፡ የሃላፊዎች አሿሿም፡ ለሹመት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፡ የኮሚሽነሮች አሿሿም/አነሳስ፡ የስራ ዘመን፡ የተቋሙ ስልጣንና ተግባር፡ የበጀት ነፃነት፡ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት/ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ያተኮረ)፡<br>- የኮሚሽኑን ስልጣን፡ ተግባራትና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፡<br>- የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም፡ ዘላቂ ማካካሻ ስርዓት አዋጅ ማርቀቅ፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፡<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፡<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፡<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፡<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤት እና ሰው ኃይል ማደራጀት ስራ፡ | ከፍትህ ሚኒስቴር፡<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ |
| 41. | የህግና ተቋማዊ ማሻሻያ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፡<br>- የልየታ፡ ማጥራት እና ማሻሻያ ስራዎችን ነጻነትን፡ ገለልተኛነትን፡ ተቀባይነት እና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ መንገድ ከመተግበር አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ ጥናት/የአውድ ትንታኔ ማከናወን፡<br>- የልየታ፡ ማጥራት እና ማሻሻያ ስርዓትን የሚመራ፡ የኮሚሽኑን ስልጣንና ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፡<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማስጸደቅ፡ የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፡<br>- አዋጁን የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፡<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤት እና ሰው ኃይል ማደራጀት ስራ፡ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፡<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምእራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 42. | አዲስ የሚቋቋሙ ሁሉም የሽግግር ፍትህ ተቋማት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን በሙሉ አቅማቸዉ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል የሚከተሉት የአቅም ግንባታ ስዎች ይሰራሉ<br>- አዲስ ለሚቋቋሙ ተቋማት አመራሮች በፖሊሲው እና ትግበራ ሂደቶች፣ በተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች ይዘት፣ በሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ሚና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን መስጠት፡ (3)<br>- አዲስ ለተቋቋሙ ተቋማት ባለሙያዎች በሽግግር ተመሳሳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን መስጠት፡ (3)<br>- የሽግግር ፍትህ ተቋማትን በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና በቴክኒክ ሊደግፉ የሚችሉ የልማት አጋሮች እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በዝርዝር መለየት፣ የባለድርሻ አካላት ልየታ (Stakeholdes Mapping) ማዘጋጀት፡ (1)<br>- በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የልማት አጋሮች እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሚኖራቸው ሚና ላይ ዎርክሾፕ ማዘጋጀት፡ (2) | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 43. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ዝርዝር የአቅም ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ፥<br>- የተቋሙ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በዓለም-አቀፍ ወንጀሎች የምርመራ እና ክስ ቴክኒካዊ አሰራር ላይ የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው አማካሪዎች መቅጠር፡ የአማካሪዎች ምልመላ/ሚና ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (2)<br>- በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ፡ በዓለም አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ እና ክስ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ቴክኒካዊ ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት ወይም ባለሙያዎችን መለየት፣ ስልጠናዎች መስጠት፡ (4)<br>- በተቋሙ ውስጥ በሰው ኃይል እና በግብዓት የተደራጀ የትምህርትና ስልጠና ማዕከል ማደራጀት፡ (1)<br>- በተቋሙ ውስጥ በአለም አቀፍ ወንጀሎች ይዘት፣ ምርምራ/ክስ ሂደት፣ እና ክስ ጉዳዮች አስተዳደር (Case Management) እና ተጎጂ-ተኮር አሰራር ላይ የስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፡<br>- የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ለማድረግ የሚያስችሉ የወንጀል ምርመራ፡ ክስ እና ማስረጃ አስተዳደር ስርዓት ማበልጸግ፡<br>- የተቋሙ አመራር እና የተመረጡ አቃብያኔ ህጎች በወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምእራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሂደት ስኬታማ ታሪክ ባላቸው የአፍሪካ እና ሌሎች አገራት የስራ ጉብኝት እና የልምድ ልውውጥ መርሀ-ግብሮችን ማመቻቸት፣ (3)<br>- የመብት ጥሰት ሰለባዎችን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ባለበት ሆኖ የወንጀል ድርጊት ጥቆማ እና ማስረጃ የሚያቀርቡበት ነጻ የስልክ ጥሪ ማዕከል፣ ድህረ-ገፅ ማደራጀት፣ (1)<br>- የተቋሙን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፣ መረጃዎች እና የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦች እና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፣<br>- የተቋሙን የስራ ሰፋት እና ውሰብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፣ | | |
| 44. | የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎት አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፡-<br>- የችሎት አመራሮች፣ ዳኞች፣ ሪጅስትራሮች፣ ተከላካይ ጠበቆች እና የተጎጂዎች ድጋፍ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ባለሙያዎችን በዓለም አቀፍ ወንጀሎች የክስ እና ክርክር መስማት፣ ችሎት አመራር፣ ውሳኔ አሰጣጥ እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣ ቅጥር ለማካሄድ፣ (2)<br>- ከላይ ለተመለከቱ አመራሮች በሽግግር ፍትሕ ሂደት የዓለም አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ፣ ክስና ክርክር፣ ችሎት አመራር፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ተጎጂ-ተኮር የፍርድ ሂደት እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይ እና አውድ-ተኮር የሰልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ ስልጠናዎች መስጠት፣ (5)<br>- የችሎት አመራሮች እና የተመረጡ ዳኞች በስኬታማነት በሚጠቀሱ የአፍሪካ እና ሌሎች አገራት፣ የሩዋንዳ የወንጀል ፍርድ ቤት (ቀድሞ ባለሙያዎች)፣ እና አለማቀፍ ፍርድ ቤት (ICC) ጉብኝት በማድረግ በሽግግር ፍትሕ የወንጀል ክስ እና ክርክር ሂደት፣ የችሎት አመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ ጉዳይ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፣ (3)<br>- የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎቶች እና እንደአስፈላጊነቱ በየክልሎች የሚደራጁ ምድብ ችሎቶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት ተደግፈው እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችሉ ግብአቶችን ማሟላት፣ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br><br>ምእራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ለዚህ የሚያስፈልግ የተፈላጊ መሰረተ-ልማት ቴክኒካል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣<br>- የችሎቱን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፣ መረጃዎችን፣ የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦች እና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፣<br>- የተቋሙን የስራ ስፋት እና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፣ | | |
| 45. | የእውነት ማፈላለግ፣ ምህረት እና ማካካሻ ኮሚሽን አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት የአቅም ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ፡<br>- በጉልህ አለም-አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ እና ክስ፣ በአማራጭ ግጭት መፍቻ መንገዶች፣ የእውነት ማፈላለግ እና ይፋ ማውጣት ስርአት፣ በምህረት እና ይቅርታ አስተዳደር እና ተመራጭ የማካካሻ ስራዎች አካሄድ ላይ ተቋሙን እና ሀላፊዎቹን የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣ ቅጥር ማካሄድ፣ (2)<br>- በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይ እና አውድ-ተኮር የሰልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ ስልጠናዎች መስጠት፣ (5)<br>- ኮምሽነሮች እና የተመረጡ የተቋሙ ባለሙያዎች በስኬታማነት በሚጠቀሱ የአፍሪካ እና ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፣ (3)<br>- ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር የተያያዙ የታሪክ መዝገቦችን፣ የተጎጂዎችን ምስክርነት ቃል እና ሌሎች ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ እና ለማቆየት የሚያስችል የኮሚሽን አርካይብ እንዲደራጅ ቴክኒካል መዘርዝር ማውጣት፣ መሰረተ-ልማቱን ማዘጋጀት፣ (1)<br>- የኮሚሽኑን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፣ መረጃዎች እና የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦችን እና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፣<br>- መረጃዎችን፣ የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦች፣ ማሳያዎች እና ሌሎች ሰነዶችን አሰብስቦ ለማቆየት እና ለትውልድ ለማስቀመጥ የሚያስችል ሙዝየም ማደራጀት፣<br>- የተቋሙን የስራ ስፋት እና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፣ | ኮሚሽን፣<br>የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 3፣<br>(ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 46. | የተቋማዊ ማሻሻያ ኮሚሽን አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፡<br>- በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የሚከናወኑ ተቋማዊ ማሻሻያ ጉዳዮች ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ እና አካሄድ ላይ ተቋሙን እና ሀላፊዎቹን የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣ ቅጥር ማካሄድ፡ (1)<br>- በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይ እና አውድ-ተኮር የስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ ስልጠናዎች መስጠት፡ (5)<br>- ኮምሽነሮች እና የተመረጡ የተቋሙ ባለሙያዎች በስኬታማነት በሚጠቀሱ የአፍሪካ እና ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፡ (3)<br>- የኮሚሽኑን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎችን እና የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦችን እና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፡<br>- መረጃዎችን፣ የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦች፣ ማሳያዎች እና ሌሎች ሰነዶችን አሰብስቦ ለማቆየት እና ለትውልድ ለማስቀመጥ የሚያስችል ሙዝየም ማደራጀት፡<br>- የተቋሙን የስራ ስፋት እና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፣ የሰው ኃይል እና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፡ | ኮሚሽን፣<br>የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ |
| 47. | በሽግግር ፍትህ አተገባበር የክልሎችን ተሳትፎ እና ሀላፊነት ዝርዝር የሚያስቀምጥ ሁሉን-አቀፍ መሪ ሰነድ (Comprehensive Guiding Document) ማዘጋጀት፡ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከክልሎች ጋር የሚፈጥረው ቅንጅታዊ አሰራር፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 48. | በክልሎች ታችኛው መዋቅር በሚገኝ ህዝብ ላይ ያተኮሩ ተከታታይ እና የተደራጁ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮች ዝግጅት እና የግንዛቤ መፍጠሪያ ስራዎች ማከናወን፡ | የሽግግር ፍትህ ጊዜያዊ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከክልሎች እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የሚፈጥረው ቅንጅታዊ አሰራር፡ | ምእራፍ 1 (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| 49. | በክልሎች ደረጃ ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ያስቻሉ የህግ ማዕቀፎች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ውስን ተቋማትን በተገቢ መልክ ለመለየት፣ ለማጥራት እና ለመለወጥ የሚረዳ ቴክኒካል ሰነድ ማዘጋጀት፣ የተቋማዊ ሪፎርም መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፣ ትግበራ መጀመር፡ | የክልል ፍትህ ቢሮዎች፣<br>መስተዳድሮች፡ | ምእራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ |
| 50. | በሽግግር ፍትህ ስራ የሚሳተፉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች መለያ እና ማሳወቂያ አሰራር፣ የሚኖራቸው ሀላፊነት፣ እና ስራቸውን | ክልሎች እና ከባቢያዊ ዩኒቨርሲቲዎች፣<br>ከሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የሚያከናውኑበትን አግባብ የሚዘረዝር ቴክኒካል ማንዋል ዝግጅት፡ | ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ጋር የሚፈጥሩት ትብብር፡ | |
| 51. | የተመረጡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ተቋማትን አቅም የመገንባት ስራ፡ | ክልሎች እና ከባቢያዊ ዩኒቨርሲቲዎች፡ ከሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ጋር የሚፈጥሩት ትብብር፡ | ምእራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ |
| 52. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ዝርዝር ስትራቴጂ ማዘጋጀት፡ መተግበር፡ | የተቋማት ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፡ እና አጋሮች ጋር በመቀናጀት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 53. | የሽግግር ፍትህ ስርአት ስራዎች የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎችን ድምፅ እና ተሳትፎ ባረጋገጠ አግባብ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መደበኛ የክትትል ስርአት (Monitoring Mechanism) ማዘጋጀት፡ መደበኛ የክትትል ስራዎች ማከናወን (2)፡ | የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቅንጅት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |
| 54. | የሽግግር ፍትህ ተቋማት አደረጃጀት የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችል የስራ ክፍል እንዲኖራቸው ማድረግ፡ | የተቋማት ጊዜያዊ/ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |
| 55. | የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መብቶች፡ ደህንነት፡ ፍትህ እና መሰረታዊ ፍላጎቶችን ከማሟላት አንፃር አስቸኳይ እና ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የሚያስችል የድርጊት መርሃ-ግብር መንደፍ፡ መተግበር፡ | የሰላም ሚኒስቴር፡ የአደጋ መከላከል እና ዝግጁነት ኮሚሽን፡ ከተቋማት ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ጋር በመቀናጀት፡ | ምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ |
| 56. | የወንጀል ተጠያቂነት ስራዎች ሂደት ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ምቹ እና አሳታፊ ማድረግ፡ ይህን የሚያግዝ ራሱን የቻለ ንኡስ መዋቅር ማደራጀት፡ | የተቋማት ጊዜያዊ/ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከኮሚሽኖች እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |
| 57. | በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የስነልቦና፡ የምክር እና የህክምና ድጋፍ የሚቀርብበት ሁሉን-አቀፍ ዘላቂ አደረጃጀት/ስርአት መመስረት፡ የፆታ ጥቃት ሰለባ አገልግሎት መሰረተ-ልማቶችን (አንድ ማእከሎች፡ ማገገሚያ ተቋማት) ማጠናከር፡ መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፡ መተግበር፡ | የተቋማት ጊዜያዊ/ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከኮሚሽኖች፡ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |
| 58. | በአጭር ጊዜ በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች (በተወሰኑ ቡድኖች ላይ ያተኮረ) የስነልቦና፡ ምክር እና ህክምና ድጋፍ የሚቀርብበት ጊዜያዊ አደረጃጀት መመስረት፡ ማጠናከር፡ ስራዎችን መተግበር፡ | የተቋማት ጊዜያዊ/ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ ከኮሚሽኖች፡ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምእራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 59. | በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ኢኮኖሚያዊ (ራስ-አገዝ) አገልግሎት የሚቀርብበት አደረጃጀት መመስረት፣ ማጠናከር፡<br>መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፡ መተግበር፡ | የተቋማት ቋሚ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከኮሚሽኖች፡ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡<br>እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምእራፍ 5፡ (ሰኔ-ነሃሴ 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ |
| 60. | የመረጃ መሰረተ-ልማት ግንባታ<br>ሀ) ድህረ-ገፅ እና ማህበራዊ ሚዲያ፡<br>- የሽግግር ፍትሕ አገር-አቀፍ ስራዎችን ሂደት፡ ረቂቆች፡ ቃለ-ጉባዔዎች፡ የምክክር ሂደቱ የምስል እና የድምጽ ሪከርዶች፡ ዋና ዋና ሰነዶች፡ ዘገባዎች እና ወቅታዊ ሪፖርቶችን የሚይዝ ድህረ-ገፅ ስራ ማጠናቀቅ፡ ከአልሚው መረከብ፡<br>- ለዚሁ ዓላማ ከፍተኛ አቅም ያለው ሰርቨር ኪራይ መፈጸም፡<br>- ድህረ-ገፁን እና ሌሎች ለሽግግር ፍትህ ዓላማ የሚከፈቱ የመረጃ ማከማቻ እና ማጋሪያ ዘዴዎችን የሚያስተዳድር፡ በየወቅቱ በአዳዲስ መረጃዎች የሚያደራጅ የሚከታተል፡ ከፍተኛ ብቃት ያለው ቋሚ የዘርፍ ባለሙያ መቅጠር፡ መመደብ፡<br>- ተመሳሳይ መረጃዎችን በተመጠነ አግባብ በፌስቡክ እና ትዊተር ገፆች ላይ ማሰፈር፡<br>- የሽግግር ፍትህ ሂደት ዋና ዋና መረጃዎችን በማእከላዊነት የሚይዝ ትልቅ አቅም ያለው መጠባበቂያ የውጭ ቋት (external database/backup drive) ማዘጋጀት፡<br>ለ) አርካይቭ<br>- የሽግግር ፍትህ ስራ ሂደቶችን የሚመለከቱ የተመረጡ በወረቀት የተዘጋጁ መሰረታዊ ሰነዶች ሚስጥራዊነት እና ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ማእከላዊ የአርካይቭ ስርአት ማደራጀት፡ ለዚህ የሚያገለግሉ ፅህፈት-ቤትና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፡<br>ሐ) ሙዚየም<br>- የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን ዝግጅት ሂደት እና የትግበራ ስራዎችን በተሟላ መልኩ የሚገልፅ በየጊዜውም እየተሟላ የሚሄድ ማሳያ (ሙዝየም) ሴክሬታሪያቱ በሚገኝበት የፍትሕ ሚኒስቴር ህንፃ ውስጥ እንዲደራጅ ማድረግ፡ | የተቋማት ጊዜያዊ ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡ | ምእራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ |
| | | | |